# የጀነቷ እንስት

## (ሑረል ዐይን)

መሐመድ ሰዒድ (ማሒ)

2011 E.C

CS CamScanner

# የጀነቷ እንስት
# (ሑረል ዐይን)


ሙሐመድ ሰዒድ

( ማሒ ME )



2011 ዓ.ል

١٤٤٠ ه

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

حقوق الطبع محفوظة

CamScanner

07 - 5 - 2013
[illegible]

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

CS CamScanner

# ማውጫ

ርዕስ


ሑረል ዐይኗን ፈላጊ ሆይ!....10
የጅንቱ አቀባበል....12
የሑረል ዐይን ትርጉም....15
የጅነቷ እንስት....15
የውበት አክሊል የተደፋባት....16
የቁንጅና ጫፍ....18
እኔን አጭተህ ትተኛለህን?....19
አንድ ለሊት በጀነት ውስጥ....21
ጣፋጭ ህልም....25
ውድ ስጦታ ከጀነቱ ሙሽራ....26
ሉዕባ ሆይ....28
የጀነቷ አበባ....30
ማራኪ ዘፈኖቻቸው....30
የአምስት ጣቶች አሻራ....32
የሑረል ዐይኗና የዱኒያዋ እንስት ተረብ....35
የምስከርነት ቃል....38
ጡባ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁን?....38
ለዱንያዋ አንበጥ ፅጌረዳ....39

ለአላህ ብሎ የተወ ምርጡን ይተካዋል ........................................ 40

ለእኛ ለሴቶችስ ........................................ 43

ተሽቀዳዳሚዎች ይሽቀዳደሙ ........................................ 43

ቃሉን ለሞላልን አላህ ምሥጋና ይገባው ........................................ 45

አንተን በመጠበቅ ላይ ነኝ ........................................ 50

ሑረል ዐይኗ በዱኒያ ንፋስ ላይ ........................................ 52

የማይገለፁ በሰው ልጅ አንደበት ........................................ 56

የሙእሚን ሽልማቱ ........................................ 57

ስለምቴው ከሑሯ ጋር ........................................ 59

ይህን ልጅ አጥበህ ቅበርልኝ ........................................ 59

የታቢዕዩ ዱዓ ........................................ 60

ሑረል ዐይኗን ፍለጋ ........................................ 61

የዱንያ አስራ አንዱ ወንዶችና ባህሪዎቻቸው ........................................ 64

ትሰሩት በነበረው ጀነትን ወረሳችሁ ........................................ 68

አላህን እንወዳለን ባዮች በበዙ ጊዜ ........................................ 69

አትሌቱ አሞራ ........................................ 72

ዋቢ መፅሐፍት ........................................ 73

CamScanner

# ምስጋና

ለተሰራለት መልካም ነገር ሰውን ያላመሰገነ አላህን ለማመስገን አይሳካለትም፡፡

አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ለሃያሉ ጌታዬ አላህ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሰው፡፡

ፅሁፌን አይተህ በማበረታታትና በትዕግስት በማረም ከጎኔ ለነበርከው ስምህን መጥቀስ ለጊዜው ይቆየኝና ከእውነተኛው የወንድምነት ጎተራ በማይለካ፣ በማይቆጠር መጠን የለሽ ፍቅር የተትረፈረፈ ምስጋናዬ ባለህበት ቦታ ይድረስ ላደረግክልኝ ሁሉ ጀዛከላሁ ኸይረን ብያለሁ፡፡

CamScanner

# እማ ቀብል

እንደ መልካም ስራዬ ማነስ ሳይሆን እንደፈድልህ ብዛት ኒዕማህን በእኔ ሆይ እየፈሰስክ ቀጥሬ ለማልዘልቀው! እመስግኔ ለማልጨርሰው !ውለታህ ጌታዬ ላህ ምስጋና ይድረስህ

# እማ በዕድ

እያንዳንዱን የህይወቴን ምዕራፍ በፍቅር ጋርደሽ ለዚህ ላበቃሽኝ ሰጎን ይኗን ከእንቁላሏ ላይ ለሰከንድ ብታነሳ ፍሬዋ እንደሚበላሸው ሁሉ እንቺም ልጅነት እስከ አሁን ምልከታሽን ከእኔ ላይ ሳታነሺ በመጠን አልባ ፍቅርሽ ድጌ ለዚህ በቃሁ ::

ከአንደበት ሲወጣ እስደሳች ቃል እናት

ውብና ከፍተኛ ደስታን የሚሰጥ መጠሪያ እማዬ!

ማይነጥፍ እዝነትሽ የምታጠቢኝ ብቸኛ ፍጡር ሆይ! አላህ ጀነተል ፍርደውስን ወፍቅሽ ::

ሳልህፍዝ ብቀር ገርፈህ ሳይገባኝ ቢቀር አስረድተህ ዲኔን አጥብቄ ንድይዝ አድርገህ እዚህ ላደረስከኝ አባዬ ምስጋናዬ ወደር የለውም በጀነተል ርደውስ አላህ ያገናኘን ዘንድ የምንግዜም ዱዓዬ ነው

# መግቢያ

ጀነትን ለሙእሚኖች ማረፊያ ትሆን ዘንድ ላዘጋጀ በውስጧም ውብና ፅዱ እንስቶችን ለፈጠረ ለታላቁ ጌታችን ለአላህ ምስጋና ይገባው፡፡ ከአክብሮት ጋር የተቀናጀ ሰላትና ሰላም በነቢያት መደምደሚያ በሆኑት ሙሐመድ صلى الله عليه وسلم ላይ ይሁን፡፡

በርካቶች ከሉል የተሰራችውን እንደመስታወት የምታንፀባርቀውን የጀነቷን እንስት ሑረል ዐይንን ወደ ጎን ችላ በማለት ከጭቃ የተሰራችውን የዱንያዋን ሴት አስበልጠው በሐራም ነገር ላይ ሲጨማለቁ የሚጨብጡት ጠፍቷቸው፣ የብስ ላይ ሉል ፍለጋ እንደወጣ ሰው ከንቱ ልፋታቸው በዱኒያም በአኺራም ፍሬ ሳይዝ ቀልባቸው ተሰብሮ ባዶ እጃቸውን ከስረው መመለሳቸውን ስመለከት፣ ማንቂያ ደውል ይሆናቸው ዘንድ እንዲሁም ሑረል ዐይንን ለማግኘት በዒባዳቸው ላይ ጠንክረው ለሚሽቀዳደሙ ሙእሚኖች ማበረታቻ እንዲሆናቸው  በማሰብ ይህቺን አጭር ልብ አንጠልጣይ ፅሁፍ በስጦታነት ለማበርከት ወደድኩ፡፡

ፀሐፊዎች ስለጀነቷ እንስት ሑረል ዐይን ሲፅፉ ብዕራቸውን ሲያነሱ ቃላቶች በፍፁም አንተባበርም በሚል አድማ ብዕራቸው ላይ ተሳልቀው ድራሻቸው ይጠፋል፡፡

CamScanner

አላህ ለባሮቹ ያዘጋጀላቸውን ዓይን አይቶ ጆሮ ሰምቶ የማያውቀውን የውበትን ጫፍ መጨረሻ በአእምሯችን ብናስብም ቁንጅናዋን ለመሳል ቃላቶችን ብንሰካካም ፈጽሞ ከአእምሮአችን አሳቤ በላይ ውበትና ቁንጅና ያላትን ሑረል ዐይንን ለመግለጽ ብዕሬን ከወረቀት ጋር አገናኘሁ።። ቃላቶች ግን ብዕሬ ላይ ተንተባተቡ።። ይህችን የጀነት እንስት በእጃቸው ለማስገባት የበርካቶችን ልፋትና ድካም ጉጉትና ፍላጎት ጫፍ መድረሱን ስመለከት ዝምታውን በመስበር ፅሑፌን ዳር ለማድረስ ተጋሁ።።

አላህ سبحانه وتعالى ወንጀሌን እንዲምርልኝና ጀነተል ዓድንን እንዲወፍቀኝ በመከጀል እንሆ ይህቺን እጭር መፅሐፍ ለሙስሊሙ ማህበረሰብ ለማበርከት በቃሁ።። አላህ ወደ ቀልብዎ የምትደርስ ያድርግልኝ።።

**ሙሐመድ ሰዒድ**

وَحُورٌ عِينٌ [٢٢:] كَأَمْثَالِ اللُّؤْلُؤِ الْمَكْنُونِ

[٢٣:] جَزَاءً بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ

“ዓይናማዎች የሆኑ ነጫጭ ቆንጆ እንስቶች አሉላቸው ልክ የተሸፈነ ሉልን የመሰሉ ይሰሩት በነበሩት ምክንያት ዋጋ ይሆናቸው ዘንድ፤ (ይህንን አደረግንላቸው)”

(አል-ዋቂዓህ 22-24)



CamScanner

## ሑረል ዐይናን ፈላጊ ሆይ!

በኢራቅ ሀገር ውስጥ አላህን አብዝቶ በመገዛቱ ይታወቃል፡፡ በእስልምና አስተምህሮት የታነጸ ፤ ኢማን ወደ ልቡ የገባ ድሀ ወጣት ነበር ፡፡የእርሱ አይነት ባህሪና ጥንካሬን ሁሉም ይመኙል፡፡ አንድ ቀን ከጓደኛው ከአቡ ሱለይማን ዳረኒ ጋር ወደ መካ ጉዞን ሊያደርጉ ወስነው የሚያደርሳቸውን ቅፍለት መምጣት ይጠባበቁ ይዘዋል፡፡ ቃፊላው ደረሰና ጉዟቸውን ወደ መካ ጀመሩ፡፡ በጉዟቸው መሀል ላይ የኢራቁ ወጣት የሚያሳየው ዒባዳ አስደንቋቸዋል፡፡ እነርሱ ሲበሉ እርሱ ይፆማል፡፡ ሲተኙ ለሊቱን ወደጌታው በመዞር በቂያመ-ለይል ያነጋል፡፡ ሁኔታው ቢያስገርማቸውም ቀርቦ ምክንያቱን ለመጠየቅ ግን ማንም አልደፈረም፡፡ መካ ደርሰው ጉዳያቸውን ፈፅመው በመመለስ ላይ ሳሉ ጓደኛው አቡ ሱለይማን ከጓደኞቹ እሱን ነጠል አድርጎ "ወንድሜ ሆይ! ለዚህ ሁሉ ዒባዳ ያነሳሳህን ነገር ንገረኝ? ለማወቅ ጓጉቻለሁ" በማለት ጠየቀው፡፡ እሱም እንዲህ ሲል መለሰ፡- "አንድ ቀን ተኝቼ በህልሜ ከወርቅና ብር የተገነቡ በሱልና አልማዝ ያሸበረቁ ህንፃዎችን ተመለከትኩ፡፡ ከበሩ ደጃፍም ላይ ዓይኗ የነፃ ፀጉሯን የለቀቀች ውብ እንስት ቆማ አየሁ፡፡ የለበሰችው ቀሚስ ከሀር የተሠራና አዘራሩም በወርቅ የተለበጠና ያማረ ልብስ ነበር፡፡ እሷን በተመስጦ በመመልከት ላይ ሳለሁ ደስ በሚል ቀልብን በሚማርክ እንደበቷ- «እኔን ለማግኘት ከፈለግክ በዒባዳህ ላይ ፅና፡፡ በአላህ እምላለሁ እኔ አንተን ለማግኘት በዱዓ እየለፋሁና እየታገልኩ እገኛለሁ፡፡ የእኔ መህር የለይል ሰላትና ፆም ነው፡፡» አለችኝ እስኪተለና ወንድሜ ሆይ! በዚህ በምታየው ዒባዳ እሷን ለማግኘት በመጣጣር ላይ ነኝ በማለት መለሠልኝ፡፡

አቡ ሡለይማንም ይህንን ታሪክ ሰምቶ ካበቃ በኋላ "ይህ ሁሉ ትግል ሑረል ዐይንን ለማግኘት ከሆነ ከሑረል ዐይን በላይ የሆነውን ጀነት ለማግኘት የሚፈልግ ምን ያህል ይለፋ ይሆን?" በማለት ተናገረ፡፡

ውቧን ሑረል ዐይንን ለማግኘት የሚጓጉትን ሰዎች በተስፋ መርከብ ላይ ጭነን ያማረ ጉዞ ማድረግ ጀምረናል፡፡

## ኑ!! ተከተሉን መንገዳችንን እንቀጥል

# የጀነት አቀባበል

የአረህማን እንግዶች ከመቃብራቸው ያለምንም ድንጋጤ ተነስተው ቆመዋል

لَا يَحْزُنُهُمُ الْفَزَعُ الْأَكْبَرُ وَتَتَلَقَّاهُمُ الْمَلَائِكَةُ هَٰذَا يَوْمُكُمُ الَّذِي كُنتُمْ تُوعَدُونَ
٢١:١٠٣

**"ታላቁ ድንጋጤ አያስተክዛቸውም መላእክትም ይህ ያ ትቀጠሩት የነበራችሁት ቀናችሁ ነው እያሉ ይቀበሏቸዋል" /አል-አንቢያእ 103/**

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

**"ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! ከመቃብራቸው ሲነሱ የወርቅ ግላስን የለበሱ ክንፍ ያላቸው ነጫጭ በቅሎዎች ፊት ለፊታቸው ይቀርብላቸዋል… የጫማቸው ክር ብርሃን ያብለጨልጫል…"**

እነዚያ አላህን የሚፈሩ ባሮች በቡድን በቡድን ሆነው ወደ ጀነት በመጓዝ ላይ ናቸው

አላህም እንዲህ ይላል፡-

" وَسِيقَ الَّذِينَ اتَّقَوْا رَبَّهُمْ إِلَى الْجَنَّةِ زُمَرًا "
{٣٩:٧٣}

**"እነዚያም ጌታቸውን የፈሩት የተከፋፈሉ ጭፍሮች ኾነው ወደ ገነት ይነዳሉ" (ዙመር 73)**

የጀነቱን በር መከፈት በመጠባበቅ ላይ ናቸው በዙሪያው ተሰብስበው ቆመዋል ማንም ያላየውን ከአእምሮ አሳቤ በላይ የሆነውን ውድ ቤታቸውን በግል ቁጥጥራቸው ውስጥ ለማስገባት በጣም ጓጉተዋል፡፡

የጀነቱ ጠባቂ መላኢካ በእንግዶቹ መምጣት ፊቱ በደስታ ፈክቶ ይታያል፡፡ በእጁም የበሩን ቁልፍ ይዟል፡፡ በሩ ተከፈተ፡፡ የአረህማን ባሮች ወደተዘጋጀላቸው መስተንግዶ በማቅናት ላይ ናቸው፡፡ ከመላኢካዎች በሚሰነዘርላቸው ሰላምታ እየታጀቡ ወደ ውስጥ ገቡ፡፡

"وَقَالَ لَهُمْ خَزَنَتُهَا سَلَامٌ عَلَيْكُمْ طِبْتُمْ فَادْخُلُوهَا خَالِدِينَ..."

{٣٩:٧٣} "(የጀነት ጠባቂዎች) ዘበኞቿ ሰላም በናንተ ላይ ይሁን ተውባችሁ ዘውታሪዎችም ኾናችሁ ግቧት ባላቸው ጊዜ (ይገቧታል)"/ ዙመር፡73/

*ወደ ደስታዋ ሀገር ጀነት በሀሳባችን ገብተን በቀልባችን እንመልከታት አላህ ፈቅዶ በአካላችን እስከንገባባት ድረስ*

እግራቸው ከሚስከና ከዘዕፈራን የተሰራውን መሬትም እንደረገጠ ፊታቸው በእንባ ተሞልቶ ምስጋናን ማቅረብ ጀምረዋል፡፡

وَقَالُوا الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي صَدَقَنَا وَعْدَهُ وَأَوْرَثَنَا الْأَرْضَ نَتَبَوَّأُ مِنَ الْجَنَّةِ حَيْثُ نَشَاءُ ۖ فَنِعْمَ أَجْرُ الْعَامِلِينَ

{٣٩:٧٤}

"ለዚያ ተስፋ ቃሉን ለሞላልን የገነትን ምድር በምንሻው ሥፍራ የምንሠፍር ስንኾን ላወረሰን ለአላህ ምሥጋና ይገባው፤የሠሪዎችም ምንዳ ምንኛ አማረ" (ዙመር 74)

ሙእሚኖች ልባቸው የጓጓለት ዘወትር የሚናፍቋት ሀገራቸው ጀነትን፤ በውስጧ ከተዘጋጁላቸው ፀጋዎች ውስጥ አንዷ የሆነችውን ሑረል ዓይንን ለማግኘት ቀልባቸው ተንጠልጥሏል፡፡

የጀነት እንግዶች ወደ ውስጥ በመራመድ ላይ ናቸው፡፡ ከበስተግራ በኩል ከወተት የነፁ ጅረቶች ይፈሳሉ፡፡ ከበስተቀኝ በኩል ከወርቅና ብር የተሰሩ ህንጻዎች ይታያሉ፡፡ ፊት ለፊት ፏፏቴ አለ፡፡ በፏፏቴው ዙሪያ ውቧ እንስት ሑረል ዐይን ቆማለች፡፡ የባሏን መምጣት በጉጉት ትጠባበቃለች፡፡ በጣፋጭና ልብን በሚሰልብ ድምጿ ታዜማለች፡፡ እንደማር በሚጣፍጥ አንደበቷ እንዲህ እያለች ትዘምራለች፡፡

የዱንያ ድሎት የማይወዳደረው

ጀነት ምንኛ ያማረ ትልቅ ፀጋ ነው

ዓይኗ በጣም በናፈቀችው ውድ ባሏ ላይ አረፈ በናፍቆም ወደርሱ አመራች

"አንተን በመጠበቅ ረጅም ዘመናትን አሳለፍኩ፡፡ ሁሌም ወዳጅ፤ የማልጠላ፤ ‹ዘውታሪ› የማልሞት በቤት ውስጥ የረጋሁ አንተን ጥዬ የማልሔድ፤ፍቅሬ ውዴ ናልኝ ናፍቀኸኛል" በማለት ተጠመጠመችበት፡፡ ተቃቅፈው ጉዟቸውን ሽቅብ ቀጠሉ፡፡

በል ና ተከተል ወንድሜ! ጠ-ቶቿ እንደ ፖም ፍሬ ቀጥ ቀጥ ብለው የቆሙትን የጀነቷን እንስት ሑረል ዐይንን እንግለፃት፡፡

ቀልብህን ከፍተህ በጆሮህ ስማኝ፡፡

በዓረብኛ ቋንቋ حور ሑር የሚለው ቃል የዓይኗ ብርሃን በጣም አንፀባራቂ ጥቁረቱ ደማቅ ከወተት በላይ ነጭ ቆንጆ ማለት ሲሆን عين ዓይን ማለት ደግሞ ዓይኗ ጎላ ብሎ የሚታይ ውብ ሴት ማለት ነው፡፡

## የጀነቷ አበባ

የአላህ መልክተኛ ረሱል صلى الله عليه وسلم እንዲህ ብለዋል፡- "ከጀነት እንስቶች መካከል አንዷት ሐውራ ወደ ምድር ብትመለከት ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ብርሀኗ ያንፀባርቃል፤ ባማረ ሽታም ምድርን ባወደች ነበር፡፡ በጭንቅላቷ ላይ የምታደርገው ሻሽ ከዱኒያና በውስጧ ካለ ሁሉ የተሻለ ነው" (ቡኻሪ ዘግበውታል)

ሻሿ ከዱኒያና በውስጧ ካሉ ሀብቶች ሁሉ ውድ ከሆነ የሻሿ ባለቤት እንስት ቁንጅና እንዴት ይገለጽ ይሆን?!

አላህ በጀነት ሰዎች ላይ ሞትን ስላስወገደ እንጂ በውበቷ ምክንያት በሞቱ ነበር::

እጁን ወደ ምድር ብታወጣ ፍጥረታት በሙሉ በውበቷ በተፈተኑ ነበር::

# የውበት አክሊል የተደፋባት

የጀነቱ ሙሽራ እጅግ የተዋበ ግቢ በር ላይ ደረሰ:: የመግቢያው በር ላይ በውበት ቀለማት በውብ ሸራ ላይ ለሁሉም በሚታይ ስሙ በወርቅ ቀለማት ደምቆ ተጽፏል:: "ይህ ላንተ የተዘጋጀ ታላቅ ቤተ-መንግሥት ነው፤ በውስጡ አንተን የሚያስደስቱ የጌታህ ስጦታዎች ይጠብቁሃል" በማለት ገና ከመግቢያው ባማረ ፈገግታ አገልጋዩ ተቀበለው:: የግቢው በር ወለል ብሎ ሲከፈት በግራና በቀኝ ዊልዳን የሚባሉ ሞት የማይነካቸው እንደ ባህር ሉል የሚያንጸባርቁ የሚፍለቀለቁ ልጆች ተሰልፈው በእንኳን ደህና መጣህ ጥዑመ-ዜማ ተቀበሉት::

አዎ! እሱን ለማስደሰት የሚበላውንና የሚጠጣውን ፍላጎቱን ሁሉ አዕምሮውን እያነበቡ የሚያቀርቡለት የአላህ ፍጡሮች ናቸው::

ወደ ውስጥ መራመድ ጀመረ:: እጅግ ማራኪ በአበቦች አጸድ የተከበበ ሰገነትን ተመለከተ:: ከሰገነቱ ፊት ለፊት የተለያየ ቀለምና ይዘት ያላቸው ወንዞች ይፈሳሉ::አንዱ የወተት ሁለተኛው የማር ሶስተኛው የወይን አራተኛው ንፁህ የሆነ ውሀ:: በምድረ ዓለም ከሚታወቁት ፈጽሞ የተለዩ ጣዕምና ጥፍጥናቸው ወደር የማይገኝለት ነው:: የጀነቱ ሙሽራ አገልጋዩን "በዚህ ባለግርማ ቤተ-መንግሥት ስንት ክፍሎች አሉ? ሲል ጠየቀው:: አገልጋዩ "ቁጥራቸውን በትክክል አላውቀውም:: ምክንያቱም ከብዛታቸው የተነሣ ቆጥሬ አልጨርሳቸውም" አለው::

"እኔ በእነዚህ ለቁጥር በሚታከቱ ከፍሎች ውስጥ ስዘዋወር መንገዶቹ ይጠፉብኝና ቀልጩ እቀራለሁ:: በዚህ ከአድማስ እስከ አድማስ በተዘረጋ ህንፃና ግቢ ፍርሃት ሊሰማኝ ይችላል"

አገልጋዩም "ብዙ እሜዋች እንግዶች ይኖሩኃል በርካታ ቆነጃጅት በየከፍሎቹ በባለ አጎበር አልጋዎች መከዳዎችን ተደግፈው ይጠብቁሃል፤ የተሸፈነ የስጎን እንቁላል ይመስላሉ"በማለት አበሸረውና ጉዟቸውን ቀጠሉ

የወተት ወንዝን ተመለከተ፤ ንጹህ ወርቅ የሚመስለውን የማሩን ወንዝ እያስተዋለ ተገርሟል፤ ወይን ጠጁ በየጊዜው ወደ ብዙ ዓይነት ቀለማት ይቀያይራል::

አገልጋዩ ከሚፈሰው የወተት ምንጭ በወርቅ ዋንጫ ጨልፎ እንዲጎነጭ ጋበዘው የተሰጠውን ወተት እንደጨለጠ አዲስ ወዘናን መጎናጸፍ ጀመረ::

"ከቡር ሆይ! እዚያ ቤተ-መንግሥት ውስጥ ያንተን መምጣት በጉጉት የሚጠብቁ እንግዶች አሉ፤ ወደዛ እናምራ" በማለት ከአገልጋዩ ጋር ተያይዘው ሄዱ::

በመንገዳቸው ላይ የጀነቱ ሙሽራ የእንግዶቹን ማንነት ለማወቅ በጣም ጓጉቷል:: እነማን ናቸው ሲልም ጠየቀ::

"እነሱማ የጌታህ ስጦታዎች ናቸው፤ የአንተን መምጣት ሲጠብቁ ዘመናትን አሳልፈዋል:: ስለምን እያወራሁ እንደሆነ አልገባህም? አዎ ስለ ቆነጃጅቱ ሑረል ዐይን ነው" በማለት እንደሉል የሚያበራው አገልጋዩ መለሰለት::

ቤተ-መንግሥቱ ውስጥ ያሉትን ከፍሎች ልዩ ልዩ መንፈላሰሻና አስደሳች ነገሮችን ሁሉ ተራ በተራ አስጎበኘው::

ወደ ውስጠኛው ሑረል ዐይኖች ወደሚገኙበት ልዩ ክፍል ሲጠጉ አገልጋዩ መላኢካ "እዚያ ካንተ በስተቀር ማንም መግባት አይችልም፡፡ የጌታህ መስተንግዶ እንህ ተጀምሯል መልካም የፍቅር ጊዜ፤ የጌታህ መስተንግዶ መጀመሩ እንጂ አያልቅም" ብሎት ወደ ኋላ ተመለሰ፡፡

የጀነቱ ሙሽራ አገልጋዩን ተሰናብቶ በዝግታ ጉዞውን ማድረግ ጀምሯል፡፡ ከክፍሎቹ አንዱ አጠገብ ሲደርስ በሩን በትህትና አንኳኳ፡፡ ተከፈተለት ወደ ውስጥ ዘለቀ፡፡ የቤቱን ቁሳቁስ መመልከት ጀመረ፡፡ ወደ ሰማዩ ቀና ሲል ጣራው እንደ መብረቅ ያበራል፡፡ የአላህ ውሳኔ ባይሆን ኖሮ ዓይኑ ጠፍቶ በቀረ ነበር፡፡ ፊትለፊቱ ቆንጆ ሚስቱ ቆማለች ይህ ሁሉ ውበት የአንዲት ሴት ነው ለመሆኑ ሰው ናት መልአክ ?! በምድራዊ ህይወቱ ላይ እንዲህ ያለ ውበትን የያዘች ሴት አይቶ አያውቅም፡፡

ይህቺ የአላህ ስጦታ ስትናገር የድምጿ ለዛ ተሰምቶ አይጠገብም፡፡ ውበቷ ጊዜና ቦታን አስረስቶ አቅልን አስቶ ያሉበትን ሁኔታ ያስጠፋል፡፡

### የቆንጆና ሜፍ

በእጥፍ ጨመረ የውበቶች ሚዛኑ

የፈኩት አበቦች አፍረው ተሸፈኑ

ዕንቡጦች ከምንጩ ደንግጠው መከኑ

# እኔን አጭተህ ትተኛለህን?

ከሠለፎች መካከል አንዱ "ዛሬ ሑረል ዐይንን ብዙ ጊዜ ቁርአንን በማኽተም የግሌ አደርጋታለሁ" በማለት ቁርጠ ተነሳ ንባቡንም ጀመረ:: በመሀል እንቅልፍ አሸንፎት አሸለበ:: በህልሙም የጀነቷ እንስት እንዲህ ስትለው አየ

أتخطب مثلي وعنى تنام

ونوم المحبين عنى حرام

لأنا خلقنا لكل امرئ

كثير الصيام كثير القيام

**"የእኔን ዓይነት መሰል አጭተህ ትተኛለህን?**

**እንቅልፍ አብዝቶ መተኛት በእኛ ወዳጅ ላይ እኮ ክልክል ነው**

**እኛ የተፈጠርነው አብዝቶ ለጾመና አብዝቶ ለሰገደ ነው"**

‹‹የጀነቱ ሙሽራ የልቡ በር ተከፍቶ በሰፊ ደረቱ ላይ አስተኝቷት ንግግሯና ጨዋታዋ አስደስቶት ይሰማታል፡፡ ከሑረል ዐይኗ ጋር በመሆኑ እርካታ ተሰምቶታል››

# አንድ ለሊት በጀነት ውስጥ

በአላህ የእዝነት ሰረገላ ላይ እየጋለብን ጉዟችንን ቀጥለናል፡፡ የጀነቱ ሙሽራ ከወርቅ የተሠሩ ደረጃዎችን እየረገጠ ወደተዘጋጀለት ፎቅ አመራ፡፡ በፎቁም ውስጥ ከውጪ ውስጡ የሚታይ ከውስጥ ውጪው የሚታይ ዙሪያው በከበረ ድንጋይ ያሸበረቀ ጣራው በአልማዝ ያጌጠ ልዩ ወደ ሆነ ክፍል አቀና፡፡ በከፍሉ ውስጥ ከንፍ ያለው አልጋ አለ፡፡ ሰባት መቶ ፍራሽ ተደራርቦበታል፡፡ የብርሃን አንሶላም ከፍራሹ ላይ ተነጥፎበታል፡፡

በወርቅ የተንቆጠቆጡ ካባና ጫማውን ለብሶ ... በለሰለሰ የሀር ምንጣፍ ላይ እግሮቹን ዘርግቶ እናቱን ከለሰለሰ ትራስ ላይ አሳርፎ በተኛበት ቆንጆዋ ሚስቱ ሑረል ዐይን ዳሌዋን እያወዛወዘች መጣች፡፡ ወደሷው ሲዞር ፊቱን በጉንጮቿ ላይ እንደመስታወት ተመለከተ፡፡ ከመስታወትም የበለጠ ንፁህ ነበር፡፡ መዳፏን ሲዳብስ ከሀር የበለጠ ለስላሳ ሆኖ አገኘው፡፡ የባቷ መቅኔ ከእጥንቷና ሥጋዋ በላይ ይታያል፡፡

የውድ ሚስቱን ደረት ተደግፎ ዝርግትግት ብሎ ተኝቷል፡፡ ጣፋጭ ከሆነ አንደበቷ ማራኪ ዘፈኗን በጆሮው ስታንቆረቁርለት ልቡ ጠፍቶ በደስታ ስሜት ያዳምጣታል፡፡

በአልጋው ላይ አንገት ለአንገት ተቃቅፈው አርባ ዓመት ካስቆጠሩ በኋላ ጭንቅላቱን ወደ ላይ ከፍ ሲያደርግ ሌላኛዋ የጀነት ሚስቱ በፈገግታ ታጅባ **"አንተ የአላህ ወዳጅ ለኛስ ተራ አይደርሰንምን?"** በማለት ትጠይቃለች፡፡ ከፍ ባለ ድምፅም ትጣራለች፡፡ እሱም ማንነቷን ይጠይቃታል፡፡ እንዲህ ስትልም ትመልስለታለች፡-

"እኔ ማለት አላህ እንዲህ በማለት ከጠቀሳቸው እንስቶች መካከል አንዷ ነኝ

"وَلَدَيْنَا مَزِيدٌ" ( ٥٠:٣٥ )

**"እኛ ዘንድ ጭማሪ አላቸው"** (ቃፍ፡35)

... አልጋው በከንፎቹ ወደ እርሷ ይበራል:: እዚያ እንደደረሰም መጀመሪያ ከተመለከታት በሙቶ ሺህ እጥፍ አምራ ያገኛታል:: ዞማ ጸጉር፣ ቀይ መልከ-መልካም ቁመናዋ የሚማርክ በተለይ ዓይኗ!:: ዓይኖቹ ዓይኖቿን ሲመለከቱ ፈዘው ቀሩ:: ከኮከብም በላይ ያበራሉ:: የሚሰማው ድምጿ በደም ሥሩ ስርጾ መንፈሱን አድሶለታል:: ከሷ ጋርም ተቃቅፈው አርባ ዓመትን ያስቆጥራሉ:: ከአርባ ዓመት በኋላ ጭንቅላቱን ወደ ላይ ሲያቀና የቤቱን ጣራ ሰንጥቆ የሚገባን ብርሀን ይመለከታል:: በእይታው ባገኘው ብርሀን ተገርሞና ተደንቆ ጠባቂውን መላኢካ ይጠይቀዋል:: መላኢካውም **"የዱኒያ ሚስትህ ከጀነቷ ሑረል ዐይን ጋር ተቃቅፈህ ስትመለከት ፈገግ አለች:: የምታየውም ወደ ውስጥ ሰርጾ የገባው ብርሃን የፊት ለፊት ጥርሷ ያመነጨው ነው:: ከአንተ ጋር በድሎቱ ሀገር አብራህ ትኖራለች::"** በማለት ይመልስለታል:: እርሷን ለማግኘት ወዳለችበት አቅጣጫ ያቀናል:: ቀልብን በሚሰነጥቅ አንደበቷ "አንተ የአላህ ወዳጅ የኔ ተራ አልደረሰምን?" ትለዋለች:: እሱም ማንነቷን ይጠይቃታል:: እሷም ትመልሳለች "እኔማ አላህ እንዲህ ብሎ ከገለጻቸው መካከል አንዷ ነኝ:-

"فَلَا تَعْلَمُ نَفْسٌ مَّا أُخْفِيَ لَهُم مِّن قُرَّةِ أَعْيُنٍ" (٣٢:١٧)

**"ከዐይን ማረፊያ ለነርሱ የተደበቀላቸውን ነፍስ አታውቅም"** (ሰጅዳህ:17)

አልጋው በሮ ያለችበት ቦታ እንደደረሰም ከመጀመሪያ ቁንጅናዋ ሙቶ ሺህ እጥፍ አምራ ያገኛታል::

ውጫዊ ውበቷ ይቅር አይወራ ቁንጅናዋም በዝቷል ሁሉም እስኪቀና፡፡ አላህን በመገዛት በጾምና ሰላት ባሏን በመታዘዝ ጀነትን ለማግኘት ታግላለችና ከጀነት እንስቶች ሁሉ በላጭ ናት፡፡

ያቁት ከሚባል የከበረ ዕንቁ የተሠራ ሸዋሊያ እና አንባርን በእጇ ላይ አጥልቃ አምራለች፡፡ መዳፏ የሚጣፍጥ የሚስከ ሽታን ያመነጫል፡፡ አፈጣጠሯም ከኑር ነው፡፡ ከንፃቷና ከጥራቷ የተነሳ የባቷ መቅኔ ይታያል፡፡

በቀኝ ክርኗ ላይ እንዲህ የሚል ጥቅስ በብርሃን ብዕር ተፅፏል፡፡

(٣٩:٧٤) " الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي صَدَقَنَا وَعْدَهُ"

**"ለዚያ ተስፋ ቃሉን ለሞላልን /ጌታ አላህ/ ምሥጋና ይገባው"** (ዙመር፡74)

በግራ ከንዷ ላይም፡-

٣٥:٣٤ " الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي أَذْهَبَ عَنَّا الْحَزَنَ"

**"ምሥጋና ለዚያ ከእኛ ላይ ሐዘንን ላስወገደልን አላህ ይገባው"** (ፋጢር 34) የሚል የምሥጋና ቃል ሠፍሯል፡፡

ለትልቁ የጀነት የሐሴት ቀን ስትሉ ዱኒያ ላይ ነፍሳችሁን ላስራባችሁ፣ ላላያችሁት የሩቅ ምስጢር የዱኒያ ስሜታችሁን ለተዋችሁ፣ ባሎቻችሁን በመታዘዝ ደፋ ቀና ያላችሁ አብሽሩ ድካም በሌለበት የጀነቱ ህይወት ከቆንጆዋ ሑረል ዐይን የበለጠ ታምራላችሁ፡፡

የፊቷ ውበት ሲገለጽ ፀሐይ
ምህዋሯን ለቃ ትሄዳለች፤
ፈገግታዋ እንደ መብረቅ
ብልጭታ ያበራል" ከባሏ ጋር
ስትተቃቀፍ ፀሐይና ጨረቃ
ቢጋራ ለምድር የሰጡትን
ብርሃን ይመስላል

# ጣፋጭ ህልም

ቤተሰቦቼን ተሰናብቼ ወደ ሐጅ ጉዞ በማድረግ ላይ ነኝ፡፡ በመንገዴ ላይ ያጋጠሙኝን ውጣ ውረዶች አልፌ መካ ገባሁ፡፡ የአላህን ቤት በመዞር ላይ ሳለሁ አንድ ሰው ቀልቤን ሳበው፡፡ ወደ እርሱም ቀረብኩና የሚያደርገውን ዱዓ ለመስማት ጆሮዬን ቀሰርኩ፡፡

"ጌታዬ ሆይ! የጓደኞቼን ሐጃ ፈፅመህልና የኔን ጉዳይ ፈጽምልኝ" እያለ በለቅሶ ጌታውን ይለምናል፡፡ ከዚህ ውጪ ሌላ ዱዓን አይጨምርም፡፡ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለማወቅ ብዬ ጠየቅኩት፡፡ እሱም "ከሩሞች ጋር ለመዋጋት ሰባት ጓደኞሞች ሆነን ከሀገራችን ወጣን፡፡ ሁላችንም በጠላቶቻችን ተማረከን፡፡ ስለመሸ አንድ ከፍል አሰረውን በሩን ቆልፈው ሄዱ፡፡ በህልሜ ሰባቱ የሰማይ በሮች ተከፍተው በራፍ ላይ በእጃቸው ፎጣን የያዙ እንስቶች ቆመዋል፡፡ የጓደኞቼ አንገት ተራ በተራ በሰይፍ ሲቀላ የጀነት እንቡጥ ፅጌረዳ እንስቶቹ ተራ በተራ እየወረዱ በያዙት ፎጣ አንገታቸው ላይ ያለውን ደም ጠርገው ይመለሳሉ፡፡ በሩም ይዘጋል፡፡ አንድ የሰማይ በር ብቻ እንደተከፈተ ቀርቷል፡፡ በእድሜ ከሌሎቹ አነስተኛ ስለነበርኩ አንድ የሮም የጦር አዛዥ አዝኖ አስለቀቀኝ፡፡ ከፍቱ የሰማይ በር ላይ ፎጣ ይዛ የምትጠባበቀኝ እንስትም እንዲህ ስትል ሰማኋት:- "ምንኛ ምርጥ ነገር ነው ያመለጠህ" ዓይኔ እያየ በሩ ተዘጋ፡፡ በህልሜ ያየሁት ከስተት ጠዋት በእውን ተፈጸመ፡፡ የምታየው ዱዓም ባመለጠኝ ዕድል ቁጭት የተነሳ ዘወትር የማደርገው ነው፡፡ በማለት መለሰልኝ፡፡

# ውድ ስጦታ ከጀነቱ ሙሸራ

ለውድ ሚስቱ ለቆንጆዋ ንግሥት ሑረል ዐይን ስጦታን ሊያበረክትላት አስቧል፡፡ ከምንም በላይ ያማረና እሷን በጣም የሚያስውባትን ውድ ጌጥ ሊሰጣት ፈልጓል፡፡

ሁለት እርምጃ እንደተራመደ አገልጋዩ ያሰበውን ከአእምሮው አንብቦ የጌጣጌጥ ማስቀመጫ የሆኑ ብዛት ያላቸውን ካዝናዎችን እየከፋፈተ የሚፈልገውን እንዲመርጥ በታላቅ ትህትና ጋበዘው፡፡

ከአልማዝና ከሉል የተሰሩት ጌጣጌጦች አፍዝዘውት ለረዥም ጊዜ ሲያማርጥ ቆየ፡፡ ፈገግ አለና እፁብ ድንቅ የሆነ ከአልማዝ የተሰራ የአንገት ጌጥ በቀይና በአረንጓዴ ከፋይና ሀር የተጌጠ የፀጉር ሪቫን እንዲሁም ውብ የሆኑ ሸዋሊያና ቀለበቶችን መርጦ በመያዝ ወደ ሑረል ዐይኗ ሚስቱ ሄደ፡፡

እሷ ጋርም እንደደረሰ በስስት እየተመለከታት በፍፁም የደስታ ስሜት ተውጦ ዓይኗን እንድትጨፍን ካደረገ በኋላ ጌጣጌጦቹን አውጥቶ በአንገቷ ላይ ሐብሉን በጣቷ ላይ ቀለበቱን አጠለቀላት፡፡

ዐይኗን ልትገልጽ ስትል በእጁ ካስጨፈናት በኋላ

ሸዋሊያውን አደረገላት። ምንም እንኳ ጌጣጌጦቹ በጣም ድንቅ ቢሆኑም የእርሷ ቁንጅና በቃላት ስለማይገለጽ በውበቷ የተዋጡ መሰሉ።በዕርግጥም ተውጠዋል።

አንገቷ ሥር ከሳማት በኋላ ወደ ጆሮዋ ተጠግቶ እንዲህ አላት፦

"አንቺን የመሰለች ቆንጆ ሚስት ጌታዬ ስለሰጠኝ ምሥጋና ይገባዋል"

وَقَالُوا الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي صَدَقَنَا وَعْدَهُ وَأَوْرَثَنَا الْأَرْضَ نَتَبَوَّأُ مِنَ الْجَنَّةِ

حَيْثُ نَشَاءُ [٣٩:٧٤]

"ለዚያ ተስፋ ቃሉን ለሞላልን የጀነትን ምድር በምንሻው ሥፍራ የምንሰፍር ስንኾን ላወረሰን ለአላህ ምሥጋና ይገባው..." /ዙመር፡74/

# ሉዕባ ሆይ

ዓብደላህ ኢብኑ መስዑድ رضي الله عنه እንዲህ ብለዋል፡-

"በጀነት ውስጥ ሉዕባ የምትባል የጀነት ሴቶች ሁሉ በቁንጅናዋ የሚገረሙባት እንስት አለች፤ ትከሻዋን በእጃቸው መታ እያደረጉ እንዲህ ይሏታል "ሉዕባ ሆይ! ምንኛ ዕድለኛ ነሽ ፈላጊዎችሽ ቢያዩሽ ኖሮ አንቺን ለማግኘት ምንኛ በለፉ ነበር፡፡" በዓይኖቿ መሀልም "እኔን የሚፈልግ ጌታዬን በዒባዳ ያስደስት" የሚል ጥቅስ ተፅፏል፡፡"

እርቃን የሆኑ ሴቶችን ከመመልከት ዓይንህን የሰበርክ ከጭቃ የተሰራችውን እንስት ችላ ብለህ ከሉል የተሰራችውን ያስበለጥክ፤ አብሽር የሉዕባ ዓይነት ውድ እንስትን ታገኛለህ፡፡

የሑረል ዐይናን ጉንጮች

እንደመሰታወት ይጠቀማል፤ የባቷ መቅኔ

ከሥጋዋ በላይ ይታያል፤ ልብሷ እያረጀም

ወጣትነቷ አይለወጥም፤ ጡብ ሊዘውጂሃ

# የጀነቷ አበባ

ዓይን ዓይኑን በስስት እየተመለከተችው አጠገቡ ተቀምጣ ታፍለቀልቀዋለች:: ከማር ወንዝ ቀድታ በወርቅ ዋንጫ ታጠጣዋለች:: በፈገግታዋ ላይ ሌላ ፈገግታ ደርባበት የትናንቱን የትዝታ ድልድይ ተሻግረው ስላሳለፉት የዱንያ ሕይወት እያስታወሱ ይሳሳቃሉ:: በሚማርክ የድምጽ ቅላፄ እያወጋችው በቆነጃጅት ከንፈሮቿ እየሳመችው እንዲህ ትለዋለች:-

"የአላህ ወዳጅ ባሌ ሆይ! በጌታዬ ይሁንብኝ በጀነት ውስጥ ካንተ ያማረ ምንም ነገር አይታየኝም"

የሑረል ዐይኗ የብብት ሽታ ከአየሩ ጋር ተደበላልቀው በጋር የሚሰጡት ልዩ የጀነቱ ጠረን ልብን ይሰርቃል::

"ሑረል ዐይን መዳፏን ከሰማይ በታች ብታወጣ ምድርን በብርሃኗ ባንጸባረቀችው ነበር፤ ፀሐይም ትጋረዳለች፤ የምታደርገው የፀጉር መሸፈኛ ከዱኒያና በውስጧ ካሉት ሁሉ ይበልጣል፤ አላህ በጀነት ሰዎች ላይ ሞትን ስላስወገደ እንጂ እሷን አይተው በቁንጅናዋ በሞቱ ነበር::"

# ማራኪ ዘፈኖቻቸው

የጀነት ሰዎች በጀነት ውስጥ ባለው ረጅም ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ተደርድረው ተቀምጠዋል:: ዱንያ ላይ ስላሳለፉት ታሪክ እየተጫዋወቱና እየተሣሣቁ ሳለ አላህ سبحنه وتعالى ደስ የምትል ንፋስን ያነፍሳል:: ዛፌቱም ትነቃነቃለች:: ንፋሱን ተከትለው ይሄዳሉ:: ከወተት የነጣ ወደ ሆነ አንድ የወንዝ ዳርቻ ያደርሳቸዋል:: ዳርና ዳር ሑረል ዐይኖች በሰልፍ ተደርድረው ልብን በሚማርክ አንደበት ይዘፍናሉ:: ዘፈኖቻቸውንም ቆመው ያዳምጣሉ:: ከዘፈኖቻቸው ጥቅስ መካከል

ለከቡራን ውድ ባሎቻችን የተዘጋጀን

የዓይን ማረፊያዎች እኛ ነን

ቆንጆዎች አቻም የሌለን

ሁሌም ህያው ነን አንሞትም

ባላችንን ጥለን አንሄድም

ከእርሱ ሌላም አናፈቅርም

አቡ ኡማመተል ባሒሊይ እንዳስተላለፉት ረሱል صلى الله عليه وسلم እንዲህ ብለዋል፡-

"የአላህ ባሪያ ጀነት ሲገባ ሁለት ሑረል ዐይኖች በእግሩና በጭንቅላቱ በኩል ተቀምጠው በሚያምር ድምጻቸው ይዘፍናሉ፤ የሸይጧን መዝሙር አይደለም፡፡ አላህን እያላቁና እያመሰገኑ ያቀነቅናሉ" (ጠበራኒ የዘገቡት ሐዲሱን ሐሰን ብለውታል)

# የአምስት ጣቶች አሻራ

ሁሉም ሰው ከስሩ እንዲጠፋ አይፈልግም:: ከአጠገቡ እንዲርቅም አይሻም ስነምግባሩ ያማረ ትሁት ሰው ነው::

ከእኛ ጋር መጫወት ይወዳል:: ባህሪው ለስላሳና ገራገር ነው:: ሁላችንም እንወደዋለን:: ለእኛ ያለው ቦታ ከፍተኛ ቢሆንም የሰውነት አካሉ ተገልጠ አይተነው አናውቅም:: ከቀናቶች በአንደኛው ቀን ድንገት ራሱን ስቶ ወደቀ ሰውነቱም ተገለጠ ለምፅ የመሳሰሉ ነጫጭ ምልክቶችን በቀኝ እጁ ክንድ ላይ ተመለከትን:: ከህመሙ ወደ ሙሉ ጤንነቱ እንደተመለሰ ‹‹በምን ምክንያት ነው ይህ ምልክት በእጅህ ላይ ያረፈው? በአላህ ስም እንጠይቅሀለን ንገረን›› በማለት ጠየቅነው:: ጥያቄያችንን እንደሰማ ሁኔታው ተቀያየረ:: በጣም ያለቅስም ጀመር:: እንደ ምንም ነፍሱን ለመቆጣጠር እየሞከረ "የጠየቃችሁኝ ነገር ከባድ ነው:: ለጓደኝነታችሁ ክብር ስል እነግራችኋለው :: ሀገሬ መግሪብ ይባላል:: ከጠላቶቻችን ብዙም አይርቅም:: ተራ በተራ እየተፈራረቅን አንዴ እነሱ አንዴ እኛ እየዘመትን እንዋጋለን:: አንድ ቀን እንደ ልምዳችን ሀያ ወንዶች ሆነን በማታ ወደ ጠላቶቻችን አመራን:: ግማሽ መንገድ እንደተጓዝን ነጋብን:: የብርሃን ጭላንጭል መታየት ጀመረ:: በአቅራቢያችን ወዳገኘነው ዋሻ ለመደበቅ ተጠጋን:: ቁጥራቸው መቶ የሚደርስ የጦር መሣሪያን ያነገቡ ጠላቶቻችን ውስጥ መሽገው ነበር:: ልንዋጋቸው ሞከርን ብዛት ስለነበራቸው ማረኩን:: ጓደኞቼንም ጠፍረው አሰሯቸው::

እኔ ግን ከቁስለኞች ጋር ወድቄ ስለነበር የሞትኩኝ መስሏቸው ሳያስሩኝ ቀሩ:: አንድ ዐይኔን ጨፍኜ የሚያደርጉትን እከታተል ጀመር:: ጓደኞቼን ተራ በተራ ገደሏቸውና ጥለው ሄዱ:: ድካም ስለተጫጫነኝ እንቅልፍ አሸለበኝ:: በህልሜም ውብ እንስቶች በሰማይ በር በኩል ወረዱ:: እንደነሱ ዓይነት ቁንጅና ያለው ፈጽሞ አይቼ አላውቅም:: ይህ የኔ ድርሻ ነው እየተባባሉ በጠላት እጅ በአላህ መንገድ የተሰው ጓደኞቼን

እየዳበሱ ተመልሰው በወጡበት በር ይገባሉ:: የኔ ተራ ደረሰና ከንዴን ስትጨብጥ እንዳልሞትኩ አወቀች እስካሁን ምን ትጠብቃለህ ? ብላ ትታኝ ሄደች"

ይህንን ታሪክ ከነገረን በኋላ ልብሱን ዝቅ አድርጎ ጡንቻውን ገለጠልን ከወተት የነፁ የአምስት ጣቶች አሻራን በከርኑ ላይ ተመለከትን::

የሰውነት ቅርጿ፤ የቆዳ ቀለሟ፤ ተክለ ሰውነቷ ያፈዛል፤ የማይጠወልግና የማይረግፍ ውበትን አላህ አጎናጽፏታል፡፡

‹‹በድንኳኖች ውስጥ የተጨጎሉ የዓይኖቻቸው ጥቁረትና ንጣት ደማቅ የሆኑ እንስቶች ናቸው››

(አር-ረህማን 55፡72)



CamScanner

# የሑረል ዐይኗና የዱንያዋ እንስት ተረብ

## ሑረል ዐይን

እናንተ የዱኒያ ሴቶች ሆይ! ቁንጅናችን የሚያፈዝ ጸባያችን የሚማርክ በቁርአንና ሐዲስ ተደጋግመን የተወሳን ውብ እንስቶች ነን፡፡ ረሱል صلى الله عليه وسلم ስለ እኛ ያሉትን ስሙ፡-

**"አንዲት የጀነት እንስት ወደ ምድር ብትመለከት ፀሐይንና ጨረቃን ጋርዳ ምድርን በተለየ ብርሃን ባካበበች ነበር" ፡፡**

አላህም እንዲህ ይላል፡-

خيرات حسان (٥٥:٧٠)

**"ፀባየ መልካሞች፤መልከ ውብ ሴቶች አሉ"** (አል-ረህማን 55፡70)

ጌታችን አላህ ለጀነት ሰዎች ያዘጋጀን ከውቦች ሁሉ ያስበለጠን ያለ ምክንያት አይደለምና ቆንጆን ለማየት ከፈለጋችሁ ወደ እኛ መዞር ብቻ ነው ምርጫችሁ፡፡

## የዱንያዋ እንስት

"በቁንጅና ከእናንተ በሰባ (70) እጥፍ እንድንበልጥ ተደርገን ተፈጥረናል"

"ጀነትን የተጎናጸፉ የዱንያ ሴቶች ዱንያ ላይ በደከሙት ዒባዳ ምክንያት ከሑረል ዐይን በ70 እጥፍ የበለጠ ቁንጅና ይኖራቸዋል" ተብሎ በረሱል صلى الله عليه وسلم እንደበት እንደተነገረልን አትዘንጉ፡፡

## ሑረል ዐይን

እኛ በጀነት ውስጥ እጅ ለእጅ ተያይዘን ፍጥረታት ሰምቶ በማያውቀው ተስረቅራቂ አንደበታችን እንዲህ እያልን እንዘፍናለን::

እኛ ስንስቅ እኮ
የጨረቃ ገላ እስኪያልቅ ይሸረፋል
ሙሉ ፣ግማሽ፣ ሩብ እያለ ይጠፋል
ከዋከብት እንደቅጠል እግር ስር ይረግፋል

## የዱንያዋ እንስት

የዱንያ ሴቶች ሆይ! እናታችን ዓኢሻ ሑረል ዐይኖች ይህንን ሲሉ ተገርመው እናንተን ወክለው የሰጡትን ምላሽ አድምጡ ሑረል ዐይኖች እጅ ለእጅ ተያዘው በአንድነት ሲዘፍኑ የዱንያ ሴቶች ተቃቅፈው ምላሽ ይሰጣሉ::

ለጌታችን ሱጁድ ወርደናል
ጾመናል ፣ሰድቀናል
በውዱእ ፊታችንም አብርቷል
አላገኛችሁም እናንተ ይህን እድል
እልፍ አዕላፍ አይኖች እኛ ላይ ያርፋሉ
እንኳን ያዩን ቀርቶ ስለኛ የሰሙ ቆንጆ ናት ይላሉ
ውበት እና ጣፋጭ በእኛ ይመሰላሉ
ሁሌም ያዩን ለታ የማናት ይላሉ

## ሑረል ዐይን

እኛ ለባሎቻችን ስንስቅ
ኮከቦቹ
ጨረቃ ወለደች እየተባባሉ
እኛን ተጠግተው ብርሀን ተሞሉ

## የዱንያዋ እንስት

ቃላት አሳምረው
ስለናንተ ውበት አድንቀው የፃፉ
እኛ የመጣን እለት ትተዋችሁ አለፉ

## ሑረል ዐይን

ውበት ከኛ ነው ዘንበ የሚንጠባጠበው ቆንጆና ጣፋጭ ውብና መሳጭ የሚሉ ቃላቶች ሁሉ አይገልጹንም ያዩን ፈዘው ቀልባቸው ይሰረቃል :: ጨረቃ ከእኛ ትደበቃለች አይናችን ሳይኳል የተኳለ ውብ ነው:: ጡባ ሊመን ኩና ለሁ ወካነ ለና::

## የዱንያዋ እንስት

አይኖቻችንን አይተው ከዋክብት አፈሩ
ድንቄም ብርሀን ሆንን ብለው ተናገሩ
ፀሐይዋም ጠለቀች ባለችበት ቦታ
እኛን ስታይ ጊዜ ተደናግራ ፈርታ
ዓኢሻ አስከተሉና ‹‹ በአላህ እምላለሁ አሸነፍናቸው ውዷ እህቴ ሆይ በጀነት ውስጥ የሑረል ዐይኖች ሁሉ አለቃ ነሽ እንኳን ደስ አለሽ ::››

## ሁለቱ ውብ እንስቶች

ሁለት ታላላቅ ብርሀናት ቢያበሩ በምድር
ምድር ያቺን ጊዜ እንዴት ትሆን ነበር

# የምስክርነት ቃል

ኡሙ ሰለማህ " رضي الله عنها ያ ረሱለላህ صلى الله عليه وسلم የዱኒያ ሴቶች ናቸው ወይስ ሑረል ዐይኖች ጀነት ውስጥ በቁንጅና በላጮቹ? በማለት የአላህ መልዕክተኛን ጠየቀቻቸው::

ረሱልም صلى الله عليه وسلم **የዱኒያ ሴቶች ናቸው በላጮቹ"** ምክንያቱ ምንድን ነው? በማለት አስከተለች:: **"በመስገዳቸውና ባደረጉት ዒባዳ ምክንያት አላህ ፊቶቻቸውን ኑር፤ ሰውነታቸውን ሐር አለበሳቸው:: መልካቸው ነጭ፣ ልብሳቸው አረንጓዴ፣ ማበጠሪያቸው ወርቅ፣ እጣን ማጨሻቸው ሉል ጌጦቻቸው ሁሉ ውብ ነው"**

እንዲህም ይላሉ: **"እኛ ዘወትር ነዋሪዎች ነን፤ ሞት የማያውቀን የማናረጅ ወጣቶች ነን"**

طوبى لمن كنا له وكان لنا

**"እኛ ለርሱ የሆንን፤ እሱም ለኛ የሆነ የጀነቱ ሙሽራ ደስታው ምንኛ አማረ፤ ጡባም ለርሱ ሆነ"**

## ጡባ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁን?

በጀነት ውስጥ የሚገኝ የወርቅ ዛፍ ነው:: የጀነት ሰዎች ልብስም ከሱ ነው የሚሰራው:: ጥላው መቶ ዓመት በፈጣን ፈረስ ያስኬዳል:: ለማን እንደሆነ ታውቃላችሁ? እስቲግፋርን ለሚያበዙ ሰዎች ነው::



CamScanner

## ለዱኒያዋ ዕንቡጥ ፅጌረዳ

ዐይን ውስጥ የምትገባ ከጨረቃ ደምቃ

ውብትስ እሷ ናት የምትታይ ልቃ

ሳቋ ሞገስ አለው ከፀሐይም በላይ

ስትስቅ ይቀናሉ ከዋከብተ-ሰማይ

## ለጀንነቷ ሙሸራ

አንቺም የሷ አምሳል ነሽ በጣም የቆነጀሽ

ዓይን ውስጥ የምትገቢ ከፍጡራን ደምቀሽ

አንደበት የምታስሪ በፍጹም ውበትሽ

# ለአላህ ብሎ የተወ ምርጡን ይተካዋል

ሙሐመድ ኢብኑ ዓብዱልባቂ ስለአጋጠመው አንድ ክስተት በራሱ አንደበት እንዲህ ሲል ይተርክልናል፡፡

"የአላህ ጥበቃ በማይለያት መካ አቅራቢያ እኖር ነበር፡፡ ከእለታት በአንደኛው ቀን ከባድ የሆነ ረሃብ አጋጠመኝ፡፡ ርሃቤን የሚመክትልኝ፣ ጉሮሮዬን የሚደፍንልኝ አንድ ጉርሻ ግን አላገኘሁም፡፡ 'ቤት ተቀምጬ አንጀቴ ከሚላወስ ወደ ውጪ ወጥቼ ብዟዟር አንዳች ነገር አገኝ ይሆናል ብዬ በማሰብ ከቤት ወጣሁ፡፡ በመንገድ ላይ ሳለሁ በሀር ጨርቅ የተጠቀለለ በውስጡም ጠጣር ነገርን ያቀፈ ከረጢት በማግኘቴ ደስ አለኝ ፡፡ ወደ ኪሴ ከትቼ ምን ሊሆን ይችላል ብዬ እያሰላሰልኩ ከቤቴ ደጃፍ ደረስኩ፡፡ በሩን ከፍቼ ወደ ውስጥ ገባሁ ቋጠሮውን ፈታሁ በውስጡ አይቼው የማላውቀው በጣም ውድና ውብ እንቁ ነበር፡፡ ርሀብ ስላሽመደመደኝ እና ስላዳከመኝ ከፊሉን ሸጬ በማገኘው ገንዘብ ምግብ ለመግዛት አስቤ ከቤት ወጣሁ፡፡ መንገዴን ይዤ ሸቅብ በመጓዝ ላይ ሳለሁ አንድ እድሜው የገፋ አዛውንት ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ሰማሁት፡-

"የሀር ጨርቅ ቋጠሮ ላገኘና ለመለሰልኝ አምስት መቶ ዲናር ለውለታው እከፍለዋለሁ" በእጁም ከጨርቅ የተሰራ የገንዘብ መያዣ ከረጢት ይዟል ንግግሩን እንደሰማሁ ለነፍሴ እንዲህ አልኳት:-

"ርቦኛል ግን ብሩን ተቀብዬ እንቁውን ብመልስ ተጠቃሚ ነኝ ግን ብሩንስ ለምን እቀበለዋለሁ ለምን ለአላህ ብዬ አልመልስለትም" በማለት አሰብኩኝ:: ይገኘው ወደ ቤቴ ሄድኩ:: የቋጠሮውን ከር ዓይነት፣ የጨርቁን ቀለም፣ የእንቁውን ልዩ ምልክት ጠይቄው መለስኩለት:: እሱም አምስት መቶ ዲናሩን ሊሰጠኝ እጁን ዘረጋ:: እኔ ግን የሰራሁት ለአላህ ነው፤ ብር አልፈልግም:: ወረታን አልቀበልም አልኩት:: ቢያስጨንቀኝም አልቀበልም ብዬ በአቋሜም ፀናሁ::

ከዓመታት በኋላ ከመካ ወጥቼ በመርከብ ጉዞ ማድረግ ጀመርኩ:: መሀል መንገድ ላይ መርከቧ ተሰበረችና ሰዎች ሰጠሙ ብዙ ገንዘብ ወደመ:: እኔም በአንድ የመርከብ ስባሪ እንጨት ላይ ተንጠልጥዬ ወዴት እንደሚወስደኝ ሳላውቅ ጉዞን ተያያዝኩ:: በባህር ውስጥም ለትንሽ ጊዜ ያህል ከቆየሁ በኋላ ንፋስ እያወዛወዘ ወደ አንድ መንደር ጥግ ወስዶ ጣለኝ:: .....በአንድ መስጂድ ውስጥም ገብቼ ቁርአንን በመቅራት ላይ ሳለሁ አንድ ግርማ ሞገስ ያለው ወጣት ጠጋ ብሎ ቁርአንን እንዳስቀራው ጠየቀኝ:: አስተምሬው እንደጨረስኩ የተለያየ ይዘት ያላቸውን ፅሑፎች ከመደርደሪያ ላይ አንስቼ ማንበብ ጀመርኩ::

ወጣቱ መፃፍ እንደምችል ጠይቆኝ ፅሑፍ ማለማመድ ጀመርኩ:: ብዙ አባቶች ልጆቻቸውን እንዳስተምርላቸው ወደ እኔ ማምጣት ጀመሩ:: ጠቀም ያለ ስጦታም ይመጣልኝ ይዟል:: ከወራት በኋላ ከማስተምራቸው ሰዎች መካከል አንዱ ጠጋ በማለት እንዲህ ሲል ሀሳብ አቀረበልኝ:- "እኛ ዘንድ የቲም ቆንጆዬ ልጃገረድ አለች፤ ከዱንያ ጥቅማ ጥቅምም በውርስ የያዘችው ከበቂ በላይ ገንዘብ አላት ልናጋባህ ወስነናልና ተቀበለን" እኔም እሺታዬን ገለጽኩላቸው:: የጋብቻ ቀናችን ተቃርቦ እሷን አስተካክለውና ሞሽረው ከጨረሱ በኋላ ወደ እኔ ይዘዋት መጡ ::

በጣም ተይዛና ተውባ ነበር:: ከሷ ውበት ይልቅ አንገቷ ላይ የተንጠለጠለው እንቁ ትኩረቴን ሳበው:: ሰዎቹም ታዝበውኝ ኖሮ ወደኔ ተጠግተው እይታህ ሙሉ በሙሉ ከእሷ ይልቅ አንገቷ ላይ ባጠለቀችው ውድ ጌጥ ላይ ነው:: ቀልቧ እንዳይሰበር ተጠንቀቅላት እንጂ በማለት ተናገሩኝ:: እኔም የዚያን እንቁ ታሪክ አጫወትኳቸው:: ደስታቸው እጥፍ ድርብ ሆነ ከመሀከላቸው አንዱም ድምፁን ከፍ አደርጎ "የዚህ እንቁ ባለቤት እንዲህ ይል ነበር:: በዱኒያ ላይ ይህን ጌጥ ከመለሰልኝ ሰው የበለጠ እውነተኛ አላህን የሚፈራ ሙስሊም እስካሁን አላጋጠመኝም:: ጌታዬ ሆይ አገናኘኝና ልጄን ልዳረው እያለ አላህን በተደጋጋሚ ሲለምን ሰምቼዋለሁ" በማለት በደስታና ፈንጠዚያ ጋብቻው እንዲጠናቀቅ አደረገ::

قال رسول الله صلى الله عليه وسلم:-

"من ترك لله شيئا عوضه الله خيراً منه"

**"ለአላህ ብሎ አንድን ነገር የተወ የተሻለውንና በላጩን አላህ ይተካዋል"**

## ለእኛ ለሴቶችስ

ጀነት ውስጥ ለወንዶች ሑረል ዐይን ሚስቶች እንዳሏቸው ሁሉ በዱንያ ህይወቷ ላይ መልካም የሆነች ሚስት በአኼራ ከሑረል ዐይን በላይ ትሆናለች ጠረኗም ተፈላጊነቷ ም ከጀነቷ አንጻት የበለጠ ይሆናል ::

በዱንያ ላይ ያላገቡት ሴት ጀነት ውስጥ የምትደሰትበትን የዓይን ማረፊያ የሚሆናትን ባል አላህ ይሰጧታል::

አላህ የጀነትን ሰዎች ደስታና ፀጋን አስመልክቶ እንዲህ ይላል:-
‹‹በውስጧም ነፍሶች የሚከጅሏት :አይኖችም የሚደሰቱበት ሁሉ አለ::
እናንተም በውስጧ ዘላለም ዘውታሪዎች ናችሁ::››
(ዙኽሩፍ 71)

## ተሽቀዳዳሚዎች ይሽቀዳደሙ

ውዷ እህቴ! የሑረል ዓይንን የቁንጅና ውበት በአጥፍ ለመብለጥና በአርረህማን ጀነት ውስጥ በሚደረገው የሥነ-ውበት ውድድር ላይ በአንደኛነት ደረጃ አማላይ ቆንጆ ለመሆን በሒጃብሽ፣ በኢማንሽና በህያእሽ ላይ ጠንክሪ ባልሽን ታዘዢ ከአጉል ባህሪያት ራቂ::

ሙዓዝ ኢብኑ ጀበል رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ ረሱል صلى الله عليه وسلم እንዲህ ብለዋል:-

"የዱንያ ሚስቱ ባሏን ስታስቸግር በጀነት ውስጥ የተዘጋጀችለት ሑረል ዐይን ሚስቱ አላህ سبحانه وتعالى ያዋርድሽ አታስቸግሪው አንቺ ጋር በእንግድነት ነው የመጣው የሚለይሽም ቀን ቅርብ ነው" በማለት ትረግማታለች::

(ቡኻሪ ዘግበውታል)

# ሑረል ዐይን

በምድር ባህር ላይ አንዴ ብትተፋ የባህሩ ጨውነት ጠፍቶ ወደ ጥፍጥና በተለወጠ ነበር፡፡ ስትጠጋት ውበቷ ከሰባ እጥፍ በላይ ይጨምራል፡፡

# ቃሉን ለምላልን አላህ ምሥጋና ይገባው

ራፊቅ ኢብኑ ዓብደላህ ዘግቦታል። ሐሻም ኢብኑ የህያ ያወራው ነው።

በሰላሳ ስምንተኛው ዓመተ ሂጅራ ሩም ሀገር ዘመትን። በዘመቻው ወቅት የሙስሊሙን ሠራዊት ምግብ የምናዘጋጀውና ጥበቃ የምናደርገው ተራ በተራ እየተቀያየርን ነበር። ከኛ መካከል እጅግ ዒባዳን የሚያበዛ አላህን የሚፈራ ቀኑን በጾም ለሊቱን በሰላት የሚያሳልፍ ሰዒድ ኢብኑ እልሐርብ የሚባል ሰው ነበር። ለሊቱን በመቆም ስለሚያሳልፍ ቀኑንም ስለሚጾም ይደከመዋል ብለን እንጨነቅለታለን። እሱ ግን የኛን ጭንቀት ቦታም አይሰጠውም። እንዲያውም በጥንካሬ ከሁላችንም በልጦ በሁሉም የሥራ መስክ ውስጥ ቀድሞ የሚታይ ሆኖ አገኘነው። ቀን ሌት ሳይል ሁልጊዜ ጠንክሮ ሲሰራ ሳየው ሁኔታው እጅግ ይገርመኝ ነበር። ከዚህም የተነሳ ራሴን እጅግ አድርጌ ናቅሁኝ።

ከቀናቶች በአንደኛው ቀን ከሱ ጋር ተረኛ ምድብተኛ ሆኜ እየጠበቅን ሳለ ከባድ ጥቃት ገጠመን። በዚያች እጅግ ፈተና በበዛባት ቀውጢ ምሽት በሰዒድ ላይ ያየሁት ትዕግስተኛነትና ጥንካሬ ከሰው ልጅ አቅም በላይ ሆነብኝ።

...ሰዒድ እንቅልፍ በዓይኑ ሳይዞር ነበር የነጋበት፡፡ ይህንንም ባስተዋልኩ ጊዜ ትንሽ እረፍት እንዲወስድ አግባብቼ አሳመንኩት፡፡

ከአንዲት ትንሽ ጎጆ ስርም ሄዶ ተኛ፡፡

ጓደኞቻችን በጦር ግንባሩ ቦታ ቦታቸውን ለመያዝ ከካምፑ ርቀው ሄደዋል፡፡ ምግብ የማዘጋጀቱ ሥራ ተራ የኔ ስለነበር ከነሱ ተነጥዬ ቀረሁ፡፡

ምግብ በማዘጋጀት ላይ ሳለሁ ከጎጆ ቤቱ አካባቢ የሆነ ንግግርን ሰማሁ፡፡ በዚያ አካባቢ ያለው ሰዒድ ብቻ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ እሱም ቢሆን ተኝቷል፡፡ እኔ ሳላይ ሌላ ሰው መጥቶ ይሆን አልኩና ወደ ጎጆው አመራሁ፡፡ ከተኛው ሰዒድ በስተቀር በአካባቢው ማንንም ማየት አልቻልኩም፡፡ ሳየው በእንቅልፍ ልቡ እያወራ ፈገግ ይላል፡፡ ይበልጥ ተጠጋሁና የሚለውን ለማዳመጥ ሞከርኩ፡፡ የሆነ ነገር እንደሚቀበል ሰው እጁን ዘረጋ፡፡ በደማቅ ፈገግታም እጁን ወደነበረበት መለሰ፡፡ እንዲህም ሲል አንሾካሸከ፡፡ “እሺ ማታ!”



CamScanner

ይህን እንዳለ ከእንቅልፉ ባኖ ተነሳ:: በፍርሃት ይንቀጠቀጥ ነበር:: እንዲረጋጋ በማሰብ ወደ ደረቴ አስጠግቼ አቀፍኩት:: እሱ ግን እየደጋገመ ላ ኢላሀ ኢልለላሀ አላሁ አክበር አልሐምዱሊላሀ ይላል::

ምን ሆንክ? ምን አገኘህ? በእንቅልፍ ልብህ ስትሰራ ያየሁት ይገርማል:: የምታወራውም ይደንቃል:: ምንድን ነው ነገሩ? ምን ዓይነት ህልም ነው ንገረኝ አልኩት:: እኔም ተደናግጬ ነበር:: በህልሙ ያየውን ታሪክ እንዲህ ሲል አጫወተኝ:-

"ቁንጅናቸውም ሆነ አለባበሳቸው ለየት ያሉ ሁለት ሰዎች ወደኔ መጡ፤

ሰዒድ ሆይ! አብሽር ሀጢአትህ ተምሯል:: ጥረትህ ሁሉ ተመስግኗል፤ ሥራህም ተቀባይነትን አግኝቷል፤ ዱዓህም ተሰምቷል፤

በህይወት እያለህም የእንኳን ደስ ያለህ መልእክት መጥቶልሃል፤ በል አሁን ተነሳና አላህ ያዘጋጀልህን የጸጋና የድሎት ዓይነት እናሳይሃለን፤ ተነስ አብረን እንሂድ አሉኝ:: አብሬያቸው መጓዝ ጀመርኩ:: ወንዞችና የአትክልት ሥፍራዎችን ሁሉ ተዟዙሬ ጎበኘሁኝ:: የጀነት ፎቅ ውስጥ አስገቡኝ:: በፎቁም ውስጥ ካለው አንድ ክፍል ወሰዱኝ:: በክፍሉ ውስጥ አልጋ አለ:: በአልጋውም ላይ የጀነቷ እንስት ተንጋላለች:: አቤት ቁንጅና እንቁ ነበር የምትመስለው:: አንተን የመጠበቁ ጊዜ ረዘመብኝ እኮ' አለችኝ::

በፈገግታ እንዴ የት ነው ያለሁት አልኳት::

አሁንማ በጀነት ውስጥ ነህ በማለት መለሰችልኝ::

አንቺስ ማነሽ ብዬ ጠየኳት::

እኔማ አላህ ላንተ ያዘጋጀኝ ባለቤትህ ነኝ አለችኝ::

እጄን ወደሷ ዘረጋሁ::

በርህራሄ እጄን ገፍታ መለሰችው:: "ዛሬ አይደለም" አለችኝ:: ዛሬ አይደለም ገና ወደ ዱኒያ ትመለሳለህ አለችኝ ደግማ:: መመለስማ አልፈልግም እያልኩ አለቀስኩ::

እሷም በሐዘኔታና በተረጋጋ መንፈስ እንዲህ አለችኝ:: መመለስህማ የግድ ነው:: እዚያ ለሶስት ቀናት ትቆያለህ:: በመጨረሻም አላህ ካለ እኛ ዘንድ ታፈጥራለህ:: እሺ ማታ ይሁን አልኳት::

ይሄኮ የተወሰነና ያለቀለት ጉዳይ ነው ብላኝ ከተቀመጠችበት ብድግ አለች:: እኔም ልይዛት ብድግ ስል ለካስ የተነሳሁት ከእንቅልፌ ነበር::

አባከህ ወንድሜ በህይወት እስካለሁ ለማንም አትንገርብኝ" አደራህን በህይወት እስካለሁ ድረስ ደብቅልኝ:: አብሽር አልኩት በደስታ ሰጥሜና ስከሬ አላህ የስራህን ውጤት ነው በህልምህ የገለጸልህ አልኩት:: ሰዒድ በጧት ተነሳና ውዱዕ አደረገ:: ሰውነቱንም ታጠበ::

ሸቶ ተቀባብቶ ወደ ጦር ግንባር ወረደ:: በዕለቱ ጸመኛ ነበር:: እስኪመሽ በውጊያ ተጠምዶ ዋለ:: አመሻሽ ላይ ከጓደኞቹ ጋር ሲመለስ ሰዎች ሁሉ ተሰብስበው ስለሱ በአድናቆት ሲያወሩ ሰማሁ:: ለሚወረወሩ ቀስቶችና ጦሮች ደረቱን ሰጥቶ በውጊያ መሀል እየሰነጣጠቀ ሲሄድ ለምንም ነገር ግድ አልነበረውም::

እኔም በውስጤ ታሪኩን አውቃችሁ ቢሆን ኖሮ ትንሽ ስቃችሁ ብዙ ባለቀሳችሁ ነበር አልኩኝ:: በዚያን ቀን ማታ በትንሽ ምግብ አፈጠረ:: ለሊቱን ቆሞ ሲያለቅስ አደረ:: በሁለተኛውም ቀን ማልዶ ወደ ጦር ሜዳ ወረደ:: የዛሬውም እንደትናንቱ ነበር ጀግንነቱ::

በሶስተኛው ቀን የሚሠራውን ሁሉ ለመከታተልና ለማየት ብዬ እኔም አብሬው ወደ ግንባር ሄድኩ:: በጀግንነት ይፋለማል:: አንዱን ጥሎ ሌላን ይፈልጋል::

በዚህም ሁኔታ ላይ ሳለ ፀሐይ ለምሽቱ ቦታዋን ለማስረከብ ተቃረበች:: ለመጥለቅም አዘቀዘቀች::

ከምሽቱ ከፍ ካለው ማማ ላይ ያነጣጠረበት አንድ እሱ ያላየው ጠላት ነበር:: ሰውዬው ኢላማው ውስጥ እንደገባለት ካወቀ በኋላ ጠንካራ ቀስቱን ከምሽጉ አናት ላይ ሆኖ ለቀቀው... አልሳተውም:: ቀስቷ መሀል ደረቱን ነበር ያገኘችው:: ሰዒድም በቁሙ ወደቀ::

በሞትና በህይወት መሀል ሆኖ ያጣጥራል:: እኔም ተጠጋሁትና የነገረኝን በማስታወስ ምሽቱን በምታፈጥርበት ነገር እንኳን ደስ አለህ ብዬ አበሰርኩት::

እንደው ምናለ ከሱ ጋር ሆኜ የተዘጋጀለትን ያንን ታላቅ ድግስ አብሬው ለመቋደስ በበቃሁ ብዬ ተመኘሁ::

የታችኛው ከንፈሩን አጥብቆ ነከሰና በዓይኑ ወደኔ እያየ እንደምንም ከንፈሩን አላቆ የሚከተለውን የአላህ ቃል አነበበ:-

**"ቃሉን በእውነት አረጋግጦ ለሞላልን አላህ ምሥጋና ይገባው"**

ነፍስና ሩሁ ተላቀቀች:: ወደሚወደው ጌታው በረረች::

# አንተን በመጠበቅ ላይ ነኝ

ኡስታዜ ሡለይማን ዘንድ ገባሁ:: ብቻውን ይስቃል:: ከፊቱ ላይም ደስታ ይነበባል:: ምን ተገኘ ዛሬ ብዬ ጠየቅኩት:: እሱም:- "ለይል ተነስቼ እየሰገድኩ ሁለተኛ ረከዐ ሱጁድ ላይ ሳለሁ እንቅልፍ ወሰደኝ፤ በእንቅልፍ ልቤም ከፀሐይ የምታበራ እንስት በእግሯ ረገጠችኝና:- "ወዳጄ ሆይ! መላኢኮች ንቁ ሆነው ተሀጁድ የሚስግዱትን ሰዎች እየመዘገቡ አንተ እኔን አጭተህ ትተኛለህ? የዓይኔ ማረፊያ ሆይ! ረጅም ዓመታትን (ተሞሽሬ) ተጨጉዬ አንተን በመጠበቅ ላይ ነኝ" አለችኝ:: የሷ ንግግር እስካሁን በጆሮዬ ይመላለሳል:: ጣፋጭ አንደበቷ ነው ፈገግ ያስባለኝ:: በማለት መለሰልኝ::

ሑረል ዐይን ወደ ምድር አጭልቃ
ብትመለከት ፍጥረታት ሁሉ አፋቸውን
ይዘው ውበቷን እያደነቁ አላህን ያጠሩ ነበር፡፡
እሷን ከማየት ውጪ ወደሌላም ፈጽሞ
ባልተዘነበሉ ነበር፡፡”

# ሑረል ዐይኗ በዱኒያ ንፋስ ላይ

አቡ ወዳአ የሚባል ታላቁ ታቢኢይ የራሱን የትዳር ታሪክ እንዲህ ሲል ያጫውተናል፡-

በረሱል صلى الله عليه وسلم መስጂድ ውስጥ እውቀትን ለማግኘት የሸህ ሰዒድ ኢብኑ ሙሰይብን የእውቀት ማዕድ አዘወትር ነበር፡፡ ኡስታዙ ዘንድ የሚማሩ ተማሪዎችም ቁጥር በርካታ ነው፡፡ ሆኖም ግን ጎበዝ ተማሪ ስለነበርኩኝ ከሌሎች በተለየ ቦታ ነበረኝ፡፡የተወሰኑ ቀናቶችን ከኡስታዜ የመማሪያ ሥፍራ ራቅሁ፡፡ ኡስታዜ የታመምኩ ስለመሰለው የመኖሪያ አድራሻዬን ያፈላልግ ጀመር፡፡ ስለ እኔ ሁኔታ ቢጠይቅም ተገቢውን መልስ የሚሰጠው ማንንም አላገኘም፡፡ ስለደረሰብኝ ችግር እያጣራ ደርሱን ማስተማሩን ቀጠለ፡፡ ጉዳዬ ከፈጀው የቀናት ቆይታ በኋላ ወደ መማሪያው ሥፍራ ሄድኩ፡፡ በደንብ ሰላምታ ተለዋወጥንና በምን ምክንያት ቀናቶችን እንደቀረሁ ለምንስ እንዳልመጣሁ ጠየቀኝ፡፡ እኔም ባለቤቴ ሞታብኝ ሀዘን ላይ መቆየቴን አብራርቼ ገለጽኩለት፡፡ ከነበርንበት ቦታ ገለል አድርጎ ይዞኝ ሄደና እንዲህ ሲል ጠየቀኝ "አዲስ ሚስት ለማግባት አላሰብከምን?"

እኔም "ኡስታዜ ለኔ ዓይነቱ የቲም ሆኖ ላደገ፣ ደሃ ሆኖ ለኖረ ልጁን የሚድር ማን አለ?! ወላሒ አሁን ከሁለት ዲርሃም በላይ ሀብትም ሆነ ንብረት የለኝም" በማለት መለስኩለት:: እኔ ልጄን አድርሃለሁ በማለት ድምጹን ከፍ አድርጎ በጆሮዬ አስተጋባ:: ታላላቅ ባለሥልጣናት ልጁን ለትዳር ጠይቀውት አልሰጥም ማለቱን አውቃለሁና ይህ ቃል ከአፉ ሲወጣ ምላሴ ተኮላተፈ:: ተንተባተብኩኝ:: "የኔን ሁኔታና ምስጢራዊ የችግር ህይወቴን ካወቅክ በኋላ ልጅህን ልትድረኝ? ስል በተደናገጠና በተቆራረጠ ድምጽ ጠየቅኩት:: እሱም እንዲህ ሲል መለሰልኝ "አዎ ልጄን አድርሃለሁ **እኛ ሙስሊሞች ሃይማኖቱና ሥነ-ምግባሩ ያማረ ሰው ካገኘን ልጃችንን እንድራለን** አንተ ደግሞ በእምነትህም ሆነ በሥነ-ምግባርህ ወደር የሌለህ መልካም ሰው ነህ:: ከዛም ለምስክርነት ሁለት ሰዎችን ከመስጂድ ጠራና ሁለት ዲርሃሙን መህር አድርጎ ዳረኝ:: ልጅቱን ግን አላውቃትም:: አላየኋትምም:: በቦታውም አልነበረችም::

ከድንጋጤና ከደስታዬ ብዛት የተነሳ የምናገረውን እንኳ ማወቅ ተሳነኝ:: ከተቀምጥኩበት ተነሳሁ:: ቀኑን ጾመኛ ስለነበርኩ መስጂድ ገብቼ የመግሪብን ሰላት ሰገድኩ:: ወደ ቤቴም አቀናሁ:: የማፈጥርበትን ነገር ዘይትና ዳቦ ከፊት ለፊቴ አቀረብኩ:: ፋኖሴን አበራሁ:: ያቀረብኩትን ምግብ አንዴ ወይም ሁለቴ እንደጎረስኩ የቤቴ በር ተንኳኳ:: "ማን ነው?" በማለት ከበሩ ኋላ የቆመውን ሰው ማንነት ለማጣራት ጠየቅኩ:: "ሰዒድ" የሚል ድምጽ ሰማሁ:: በአላህ እምላለሁ

ሰዒድ በሚል መጠሪያ ስም የማውቃቸውን ሰዎች ሁሉ አሰብኩ:: ሰዒድ ኢብኑ ሙሰይብ ግን በልቦናዬም ውል አላለም ነበር:: ምክንያቱም አርባ ዓመት ሙሉ ቤቱ ወይም መስጂድ እንጂ ሌላ ቦታ ታይቶ አይታወቅም:: አወለ ሰፍ እንጂ የሰውን ጀርባ እያየ ሰግዶ አያውቅምና ነው:: በሩን ከፈትኩ:: ከፊት ለፊቴ ሰዒድ ኢብኑ ሙሰይብ ቆሟል:: በቃ ልጁን ለኔ ዓይነቱ መናጢ ደሃ በመዳሩ ተጸጽቶ ሀሳቡን ሊቀይር ነው የመጣው ስል አሰብኩ:: የሙሐመድ አባት ሆይ! ሰው አትልክብኝም ያለሀበት ቦታ እመጣ ነበር አልኩት:: እሱም "በፍጹም ዛሬማ እኔ ራሴ አንተ ዘንድ ልመጣ ይገባል" በማለት መለሰልኝ ወደ ቤት እንዲገባ ጋበዝኩት:: "አይ አልገባም ባይሆን የመጣሁት ለጉዳይ ነው ልጄ የአንተ ሚስት ሆናለች እሷ አባቷ ቤት ብቻዋን አንተም በቤትህ ያለ አጫዋች ስለ እሷ እያሰብክ ብቻህን መሆናችሁን ጠልቼ ይዣት መጥቻለሁ አለና" ከጎኑ ቆማ ወደነበረችው መልከመልካም ውብ እንስት ዞሮ "ልጄ ሆይ! በአላህ ስምና ረድኤት ወደ ባልሽ ቤት ግቢ" በማለት ትዕዛዝን ሰጣት:: ከእፍረቷ የተነሳ ወደ እኔ ስትመጣ ቀሚሷ አደናቅፏት ልትወድቅ ተቃረበች::

አባቷን እንኳ ሳልሰናበት ከፊቷ ተቀድሜ እየመራኋት ወደ ቤት ገባን:: ድህነቴ ስላሳፈረኝ ዳቦና ዘይቱን ደብቅኩ:: የፋኖሱን ብርሃንም አደበዘዝኩ:: ጣራ ላይ ወጥቼ "ሰዒድ ልጁን ዳረኝ እቤቴ ድረስም ይዞልኝ መጣ" ብዬ ከፍ ባለ ድምጽ ጎረቤቶቼን ተጣራሁ:: ከጎረቤቶቼ ሰዎች መካከል አንዲት አሮጊት እንዲህ አለች

"አንተ ሰው! ለመሆኑ የምትናገረውን ታውቃለህ? ሰዒድ ልጁን ድሮህ ከቶውንም ቤትህ ድረስ ይዞልህ ሊመጣ?! የእሷ ነገር እኮ እንኳን ላንተ ለደህው የታላቁ ባለሥልጣን ልጅ ወሊድ ኢብኑ ዓብዱል መሊክ ሽማግሌ ልኮ እምቢ የተባለበት ጉዳይ ነው እኔም "አዎ ድሮኛል ከፈለጋችሁ ግቡና ተመልከቱ:: ግቡ እቤቴ ናት ያለችው ተመልከቷት እውነተኛነቴን ታረጋግጣላችሁ" በማለት መልስ ሰጠሁ::

ከእሷ ጋር ሳምንትን ከቆየሁ በኋላ ወደ ቀድሞው የዕውቀት ገበታ ሥፍራ ዒልምን ለመቋደስ ስነሳ "ቁጭ በል አባቴ ጋር ያለው ዕውቀት ሁሉ እኔ ጋርም አለ" በማለት በጀርዬ ሹከ አለችኝ::

የረሱልን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሐዲስ የሐፈዘች የጌታዋን ቃል አከባሪ የያዘችውን ዕውቀት ተግባሪ አላህን ፈሪ የባሏን ሐቅ ጠባቂ መልከ መልካምና እጅግ በጣም ቆንጆ እንስት ሆና አገኘኋት::

# የማይገለጹ በሰው ልጅ አንደበት

ሑሯ የኔ ዓለም የውበት ሁሉ ውብ
ውበት ካንቺ ዘንቦ ደርሶ ሚንጠባጠብ
ዓይኖችሽ ይልቃል ከሰማይ ጨረቃ
አየናት በማታ ካንቺ ተደብቃ
ፀሐይም ከፊትሽ በሚወጣው ፀዳል
አየናት ስትሸሽግ ራሷን ስትከልል
ፀጉርሽም ዞማ ነው ማረፊያው ከዳሌሽ
በጥበብ ተሰርቷል ባትሽ ተረከዝሽ
ስልክክ እንዳለ ነው ቀጭኑ አፍንጫሽ
ራስን ያስታል ያ ሞንዳላ ዳሌሽ
ጣቶችሽ አለንጋ ጥፍሮችሽም ስላት
የማይገለፁ በሰው ልጅ አንደበት

# የሙእሚን ሽልማቱ

ሳቢት ኢ.ብኑ ኑዕማን ይባላል፡-

... በጣም ተርቧል፡፡ ከረሃቡም የተነሳ መላ አካላቱ ተዳክሟል፡፡ በአቅራቢያው ወዳለው አትክልት ሥፍራ አመራ፡፡ ዓይኑ ወደ አንድ የፍራፍሬ ዛፍ ተመለከተ፡፡ የተንጠለጠለችውን አንድ የፖም ፍሬ እጁን ሰዶ ቀጠፈ፡፡ ግማሹን በላና በአቅራቢያው ካለው ወራጅ ውሀ ትንሽ ተጎነጨ፡፡ የሰራው ስህተት ለአእምሮው የፀፀት ምልክትን ሰጠ፡፡ ወየውልሽ! ባለሀቁን ሳታስፈቅጂ ያንቺ ያልሆነን የአትክልት ፍሬ ትመገቢያለሽ እንዴ? በማለት ነፍሱን ወቀሰ፡፡

የአትክልቱን ባለቤት አፈላልጎ አግኝቶ ለተመገበው ፖም ይቅርታ መጠየቅ እንዳለበት ወሰነ፡፡

የአትክልተኛውን ቤት ፍለጋ ተንቀሳቀሰ፡፡ ብዙ ካጠያየቀ በኋላ ቤቱን አገኘው፡፡ ወደ ሰውዬው ቤት በር ጠጋ ብሎ አንኳኳ፡፡ ባለ አትክልቱ ገበሬም ከቤቱ ወጣ፡፡ በእጁ የያዘውን የተገመጠ ፖም ይዞ ያደረገውን ድርጊት መናገር ጀመረ፡፡ "በጣም ተርቤ ስለነበር ከወንዙ ዳር ካለው የአትክልትህ ቦታ ይህንን ፖም በላሁ፡፡ ከተመገብኩ በኋላ የኔ ሐቅ አለመሆኑን አስታወስኩ፤ይቅርታ እንድታደርግልኝና ለሰራሁት ስህተትም ተመጣጣኝ ቅጣት እንድትቀጣኝ" በማለት መማጸን ጀመረ፡፡

ሰውዬውም "የምልህን ካላሟላህ በስተቀር በፍጹም ይቅርታ አላደርግልህም" አለው፡፡ "ምንድንነው ግዴታ ያደረግከብኝ" ብሎ ጠየቀ፡፡

"ዓይነ ስውር፣ መስማት የተሳናት እንዲሁም መናገር የማትችል ልጅ አለችኝ። እሷን እንድታገባ እፈልጋለሁ" ብሎ መለሰለት።

የገባበትን አስቸጋሪ ጉዳይ በደንብ አጢኖትና አስቦበት የማይጸጸተው ውሳኔ ለማሳለፍ አሰበ።

"በግማሽ ፖም ምክንያት አላህ በጀሃነም እሳት ከሚያቃጥለኝና ዘላለም ከምሰቃይ ይህችን እንስት ማግባት የተሻለ ነው፤ በዚህች አጭር የዱንያ ህይወት መቸገሬ ከረጅሙ የአኼራ ህይወት ስቃይ እጅግ የተሻለ ነው" ሲል ከራሱ ጋር ተማከረና ጋብቻውን ተቀበለ።

የሠርጉ ቀን ሲደርስ ጋብቻውን ለመፈጸም ቤት ቀድሞ ተገኘ። እጅግ በጣም ተጨንቋል። ሀሳብ ገብቶታል።

ኒካህ ከተደረገ በኋላ ወደ ሙሽራዋ ክፍል ገባ። ሚስቱ ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ "የአላህ ሰላም ባንተ ላይ ይሁን" አለችው። ግር ብሎታል። ተሳስቶ ይሆን? ተመለከታት! የሑረል ዐይንን ሁኔታ አስታወሰ፤ ቁንጅናዋ ተመሳሰለበት።

በዝምታ ተዋጠ። ይህቺ ሴት ትናገራለች፣ ትሰማለች፣ ታያለች! ምንድንነው ነገሩ? ግራ ገብቶታል። እሷ ወዳለችበት ቦታ አመራ። አባቷ የተናገረውን ሁሉ አጫወታት። እርሷም:-

"አባቴ ያለው ሁሉ እውነት ነው አልዋሸም፤ አትናገርም ያለህ በህይወቴ የሐራም ንግግርን ተናግሬ ስለማላውቅ ነው፤ መስማት አትችልም ያለህም ሃሜትም ሆነ አልባሌ ንግግርን ሰምቼ አላውቅም፤ ዓይነስውር ናት የተባልከውም እውነት ነው ወንድን በሐራም ተመልክቼ አላውቅምና ነው" በማለት መለሰችለት። አላህን በመፍራቱ ምክንያት አባቷ ለትዳር መረጠው። በተከበረው የፍቅር ህይወታቸው ውስጥ ኢማሙ አቡ ሀኒፋን ወለዱ።

## ሰለምቴው ከሑሯ ጋር

እስልምናን የአስር ሰላት ወቅት ነው የተቀበለው ሻወር ከወሰደና ሸሃዳን ከያዘ በኋላ ስለ ኢስላም ለማወቅ ላፕቶፑን ከፍቶ እያነበበ ለሊቱን አሳለፈ፡፡በጣም ቅርብ ጓደኛሞች ነን፡፡ የሱብሒን ሰላት ሰግጄ እንደጨረስኩ ልዘይረው ወደ ቤታቸው አቀናሁ፡፡ የለቅሶ ድምፅ ይሰማል፡፡ ስሙን እየጠሩ ያለቅሳሉ፡፡ አንድ አደጋ መከሰቱን አስተዋልኩኝ፡፡ ድንጋጤ ወረረኝ ተብረከረኩ፡፡ ወደ ውስጥ ገባሁ፡፡ አባቱን ፊት ለፊት አገኘኋቸው፡፡ ጓደኛዬ ምን ሆነ ስል ጠየቅኳቸው፡፡ "ጓደኛህ ሞቷል" አሉኝ፡፡ እንዴት ብዬ ማልቀስ ጀመርኩ፡፡ "ወደ ላይ ውጣና አሟሟቱን እይ" በማለት ያለበትን ክፍል አመላከቱኝ፡፡ በሩን ከፍቼ ስገባ ሱጁድ ላይ እንደተደፋ ነበር የሞተው፡፡ ከፍት ወደነበረው ኮምፒውተር ዓይኖቼን ስወረውር ስለ ሑረል ዐይን ቁንጅና የሚገልጽ ፅሁፍን ተመለከትኩ ለካስ ስለ ጀነቷ ፀጋ በውስጧ ለእኛ አላህ ስላዘጋጀልን እንስት እያነበበ ሳለ ነበር የሱብሒ ወቅት ገብቶበት እየሰገደ ሱጁድ ላይ የሞተው፡፡

## ይህን ልጅ አጥበህ ቅበርልኝ

የአስራ ስድስት ዓመት ለጋ ወጣት ነው፡፡ ቁርአንን ሀፍዟል፡፡ መስጂድ መመላለስ ያዘወትራል፡፡ ይህ ወጣት በጠና ታሞ ሞተ፡፡ አጎቱ ነበር የሚያስታምመው፡፡ የሞተው ማታ ስለነበር አጎቱ አጥቦ ለመቅበር ንጋትን እየተጠባበቀ ሳለ እንቅልፍ አሸንፎት አሸለበ፡፡ በሕልሙም ውብ እንስት ወደርሱ አቅጣጫ መጣችና እንዲህ አለችው፡- "በአላህ ይህን ልጅ አጥበህ ቅበርልኝ፤ ከሞተበት ሰዓት ጀምሮ እሱን በመጠበቅ እንደ ፍም እሳት እየጋምኩ የምገኝ የጀነቷ እንስት ነኝ በአላህ ይሁንብህ ባሌን በፍጥነት አጥበህ ቅበርልኝ" ታሪኩን በአንደበቱ ይቀጥልልናል፡-

"ከእንቅልፌ በድንጋጤ ነቃሁ፤ የቤቱ ሽታ በመልካም ጠረን ተሞልቶ ያውዳል፤ ጀናዛውን በማጠቢያ እንጨት ላይ ዘርግቼ ጓደኞቼን ጠርቼ ማጠብ ጀመርኩ:: በመሀል መብራት ጠፋ:: ከጓደኞቹ መካከል አንዱን ፋኖስ እንዲያመጣ አዘዝኩት:: ፋኖሱን ሊያመጣ ወጣ:: ነገር ግን በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ከጀናዛው አካል በሚወጣው ብርሀን ቤቱ በራ:: ለማገላበጥ ሳንቸገር በቀላሉ አጥበን ጨረስን:: ወደ መቃብርም አስገባነው:: ፊቱ በፈገግታ ተሞልቶ የናፈቀውን ሰው ያገኘ ይመስላል::

ومن لم يجعل الله نور فما له من النور

"አላህ ብርሀንን ያላደረገለት ሰው ለርሱ ብርሀን የለውም"

## የታቢዒዩ ዱዓ

‹‹ሙዕሚኖች በተሰበሰቡበት ቦታ ዳመና ታልፋለች፤ ምን ላዝንብላችሁ በማለትም ትጠይቃለች፤ የጠየቋትንና የተመኙትን ሁሉ ታዘንባለች፤ አላህ የዚያ ቀን ካደረሰኝ ውብ የሆኑትን ሑረል ዐይኖች አዝንቢልኝ እላታለሁ››

(ታላቁ ታቢዒይ ኻሊድ ኢብኑ ሚዕዳን)

# ሑረል ዐይኗን ፍለጋ

የአንድ ት/ቤት ተማሪዎች ለትምህርታዊ ጉብኝት ዛፍ በሚበዛበት ጭር ያለ ስፍራ አቀኑ ከረጅምና እልህ አስጨራሽ ጉዞ በኃላ የፈለጉት ቦታ ደረሱ፡፡በቡድንና በተናጥል ተፈጥሮን እያደነቁ መማር ጀመሩ ጉብኝታቸውን እንደጨረሱም አስተማሪዎች ተማሪዎቻቸውን ሰብስበው ተመለሱ፡፡ አንዲት ሊጋ ወጣት ኮረዳ ተማሪ ብቻዋን ቀርታለች እየመሸ ስለሆነ ባሱ ወደነበረበት ቦታ ሄደች፡፡ ነገር ግን ከሷ ውጪ ማንንም አላገኘችም፡፡ ሁሉም እንደሄዱ አወቀች፡፡ በዚያ ጫካ ብቻዋን መሆኗ አስጨንቋታል፡፡ በድንጋጤ ልቧ ይመታል፡፡ ከዐይኗም እንባ እንደ ጎርፍ ይወርዳል፡፡ ያላት አማራጭ ቅርብ ወደሆነው አንድ ቤት ማምራት ነበር፡፡ ከረጅም ጉዞ በኋላ ትንሽዬ ጎጆ አገኘች፡፡ ወደ በሩ በመጠጋትም አንኳኳች፡፡ በሀያዎቹ ዕድሜ መጨረሻ የሚጠጋ ወጣት በሩን ከፈተላት፡፡ ሲመለከታትም ደንግጦ አንቺ ማን ነሽ? ሲል ጠየቃት፡፡ እያለቀሰች እንዲህ በማለት መለሰች "ከአንድ ትምህርት ቤት ለትምህርታዊ ጉዞ ነበር የመጣሁት ጓደኞቼና አስተማሪዎቼ ብቻዬን ትተውኝ ሄዱ መመለሻ መንገዱንም አላውቅም" በማለት ቤቷ የሚገኝበትን አካባቢ ነገረችው፡፡ እሱም "አሁን ያለሽበት መንደር ብዙ ሰዎች የማይኖሩበት ነው፡፡ አንቺ የምትፈልጊው መንደር ከዚህ ትንሽ ራቅ ይላል መንገድ ላይ ይመሽብሽና ማደሪያ ታጫለሽ፡፡

ስለዚህ ወደ ውስጥ ግቢ:: እዚህም እደሪ:: ጠዋት መንገዱን አሳይሻለሁ" አላት:: ወደ አልጋውም እየጠቆማት እዚህ ላይ እደሪ እኔ መሬት ላይ አድራለሁ ብሎ አልጋውንና የቀረውን ቦታ በመጋረጃ ለሁለት ለየው (ከፈለው):: ልጅቷም እየፈራች ልጁ የሚሰራውን መከታተል ጀመረች:: ሰውነቷን በጠቅላላ ዓይኗን ብቻ አስቀርታ ሸፈነች:: ልጁም ኪታብ ከፍቶ ማንበብ ጀመረ:: ብዙም አልቆየም ኪታቡን በፍጥነት ዘግቶ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ሻማ ላይ አውራ ጣቱን አስቀምጦ ያቃጥለው ጀመረ:: እያቀያየረና እያፈራረቀ የተቀረቱንም ጣቶቹን አቃጠለ:: ልጅቱ በፍርሃት ደንግጣ ማልቀስ ጀመረች:: ሰው ነው ሰይጣን ግራ ገባት እንቅልፍ በአይኗ ሳይዞር ነጋ:: ጠዋት ሲነጋም እቤቷ አደረሳት:: የተከሰተውን ታሪክ ለአባቷ አጫወተችው:: ማመን አቃተው:: ሄዶ ለማረጋገጥም ተጓዥ መስሎ ወደ ወጣቱ ልጅ አመራ መንገድ እንዲጠቁመውም ጠየቀው:: የልጁን እጅ አባት ተመለከተ:: ቅዳጅ ጨርቆች ተጠምጥመውበታል:: እጅህን ምን ሆነህ ነው በማለትም ጠየቀው ልጁም እንዲህ ሲል መለሰ:-

" ከሁለት ቀን በፊት በጣም ቆንጆ ልጅ መንገድ ጠፍቷት መጥታ ነበር፡፡ እኔ ዘንድ ባለው አልጋ ላይ ተኛች፡፡ ሽይጧንም ከሷ ጋር በሀራም እንድተኛ ይወሰውሰኝ ጀመር፡፡ እኔም ይህንን ወንጀል ላለመፈጸምና በዚህ ወንጀል ምክኒያት ከባዱን የጀሀነም እሳት ለማስታወስ ጣቶቼን አንድ በአንድ አቃጠልኳቸው፡፡

በዚህች ሌት ላይ ዚና ከምፈጽም የጣቶቼን መቃጠል መረጥኩ፡፡ የጀነቷን እንስት ሑረል ዐይንን በጀነት ውስጥ ከምከለከል ጣቴ እስኪከስል መንደዱን አስበለጥኩ፡፡ አባት ተገረመ፡፡ ወደ ቤቱም በእንግድነት ጋበዘው፡፡ ልጁን ሊያጋባውም አሰበ፡፡ ወጣቷ እሷ መሆኗን ሳያውቅ ሊድረው ወሰነ፡፡ በሃሳቡም ተስማማ፡፡ አንድ ለሊት ከሷ ጋር በሐራም ከማደር ህይወቱን ሙሉ በሀላል ደስተኛ የሚሆንበትን መንገድ አገኘ የተሻለውንም አላህ መረጠለት፡፡

# የዱንያ አስራ አንዱ ወንዶችና ባህሪዎቻቸው

ከጃሂሊያ በፊት ስለነበሩና ስለባሎቻቸው ባህሪ ምንም ሳይደብቁ ለመነጋገር ስለተስማሙ አስራ አንድ ሴቶች ታሪክ ዓኢሻ ረዲየላሁ ዓንሃ ለረሱል صلى الله عليه وسلم መተረክ ጀመረች:: በባሎቻቸው ላይ ያዩትን ሁሉ ለማውራት ተስማምተዋል:: ምን አሉ ይሆን?

<u>የመጀመሪያዋ ሴት:-</u> "የኔ ባል ልክ በረጅም ተራራ ጫፍ ላይ እንዳለ የማትረባ ግመል ሥጋ ነው ከተራራው ጫፍ መድረስ በጣም አስቸጋሪ ነው:: ቢደረስ እንኳ ሥጋውም ጥሩ አይደለም" በማለት የባሏን አስቸጋሪ፣ ባህሪ እና መጥፎነት ገለጸች:: ግንኙነትም ላይ አያረካትም:: ትዕቢተኛ ነው:: ስስታምና ደሃ መሆኑን ተናገረች::

<u>ሁለተኛዋ ሴት:-</u> "እለየዋለሁ ብዬ ስለምፈራ የባሌን ባህሪ አልናገርም:: (ብዙ ችግሮች ስላሉበት ያንን ሁሉ ችግር ብታወራና ይህ ዜና ቢደርሰው ይፈታታል፣ ከርሱ ጋር የምትኖረው ለልጆቿ ስትል ነው)

<u>ሶስተኛዋ ቀጠለች፡-</u> "ባሌ ቁመቱ ረጅም ነው፤ስለሱ ከተናገርኩ እሱም ከስማ ይፈታኛል፡፡ ዝም ካልኩ በአንጥልጥል ይተወኛል" አለች፡፡ ማለትም ባሏ ረጅም ነው፡፡ መልኩም አያምርም፡፡ ጥሩ ጸባይ የለውም፡፡ ስህተቷንም ይቅር አይልም፡፡ ልክ ከላይዋ ላይ እንደተንጠለጠለ የሰላ ሰይፍ ነው፡፡ የምትኖረው በማይቋረጥ የፍቺ ዛቻ ነው፡፡ ቅሬታ ባቀረበች ቁጥር እፈታሻለሁ በማለት ያስፈራራታል፡፡ ባል ሚስቱን መያዝ ባለበት መልኩ አይዛትም፡፡ በመሆኑም በአንጥልጥል ላይ ነው ያለችው፡፡ ወይ አልተገባች ወይ አልተፈታች፡፡

<u>አራተኛዋ ሴት</u> "የኔ ባል እንደ ጢሃማ ምሽት መካከለኛ ሰው ነው፡፡ አይሞቅም አይበርድም፡፡ አልፈራውም አላዝንለትምም አለች፡፡ እንደሚታወቀው የጢሃማህ ምሽት ንፋስና አቧራ የለውም፡፡ ለነዋሪዎች ምቹ ነው፡፡ ባሏ ለሷ ጥሩ እንደሆነና ሚዛናዊ ባህሪ እንዳለው ጎድቷት እንደማያውቅ ተናገረች፡፡

<u>አምስተኛዋ፡-</u> "የኔ ባል ወደ ቤት ሲገባ አቦ ሸማኔ ሲወጣ ደግሞ እንደ አንበሳ ነው፡፡ ቤት ውስጥ ስላለው ነገር አይጠይቅም"

ወደ ቤት ሲመጣ እንደ አቦ ሸማኔ ቸርና ንቁ ነው፡፡ ከቤት ወጥቶ ከሰዎች ጋር ሲቀላቀል ደግሞ እንደ አንበሳ ጀግና ነው፡፡ ቤት ውስጥ ሚስቱን ይሄ ጎደለ ይሄ አለቀ አይልም"

<u>ስድስተኛዋ በበኩሏ፡-</u>

"የኔ ባል ምግብ አብዝቶ ይመገባል፡፡ ሲጠጣም ጭልጥ አድርጎ ነው፡፡

ሲተኛ ጥቅልል ብሎ የኔን ሐዘን ለማስቀረት እጆቹን በሰውነቴ ላይ አያንቀሳቅስም"

ማለትም ባሏ ለቤተሰቡ ብሎ የሚያስቀምጠው ነገር የለም:: ብዙ ይመገባል:: ለእገሌ ብሎ አያስተርፍም:: ሲተኛም በብርድ ልብሱ ለብቻው ተጠቅልሎ ነው የሐዘን ስሜት ሲሰማትም በእጆቹ አቅፎ አያባብላትም:: የሐዘኗን መንስኤም አይጠይቃትም::

<u>ሰባተኛዋ</u>:- "ባለቤቴ መጥፎ ሰሪ፣ ዝርክርክና ሞኝ ነው:: የሌለበት ዓይነት ጉድለት የለም:: ካወራሁት ይሰድበኛል:: ቀልድ ከቀለድኩም ጭንቅላቴንና ሰውነቴን በመምታት ጉዳት ያደርስብኛል"

<u>ስምንተኛዋ ሴት</u>:- "ባለቤቴ ሲነኩት ሰውነቱ እንደ ጥንቸል ለስላሳ ነው:: ሽታው እንደ ዘርነብ (ጥሩ ሽታ ያለው ሳር) ነው:: እኔ ከሱ በላይ ሆኜ ነው የምኖረው:: እሱ ደግሞ ከሰዎች በላይ ነው:: በማለት እንደሚቆነጃጅለት ገለፀች::

<u>ዘጠነኛዋ</u>:- "ባለቤቴ ረጅና ቸር ሰው ነው:: ቤቱ ሰፊና ሁሌም ለእንግዶች ክፍት ነው:: ለእንግዶቹ ምግብ ስለሚያበስል ከቤት እሳት አይጠፋም:: እንግዶቹን ሲያስተናግድ ብዙ አይበላም:: ቤቱን ከጠላት ወይም ከአደጋ ለመጠበቅ ለሊቱን ቁጭ ብሎ ነው የሚያድረው::

<u>አስረኛዋ ቀጠለች</u>:-

"ባለቤቴ ስሙ ማሊክ ነው ስሙ:: ማሊክ ምንድነው? ከምለው ነገር

ትልቅ ነው:: ግመሎቹ በሙሉ ቤት ነው የሚውሉት:: የቢላዋ ድምጽን ሲሰሙ አበቃልን ብለው ያስባሉ:: ለእንግዶች ማስተናገጃ ልንታረድ ነው ብለው ይሰጋሉ::

<u>አስራ አንደኛዋ፡-</u> "ባለቤቴ አቡ ዘርዕ ነው:: ስለ አቡ ዘርዕ ምን ማለት እችላለሁ? በርካታ ጌጣጌጦችን ስለሰጠኝ ጆሮዎቼ ሸክም በዝቶባቸዋል:: እጆቼ ወፍረዋል:: ዘወትር ያስደስተኛል:: ከደስታዬም ብዛት በራሴ እኮራለሁ::

ከበግ በስተቀር ምንም ከሌለው ድሃና ችግረኛ ቤተሰብ አገኘኝ:: ሆኖም ፈረሶች፣ ግመሎችና የተጣራ ሰብል ወዳለበት የተከበረ ቤተሰብ አመጣኝ:: ምንም ብናገር አያመናጭቀኝም:: ስተኛ እስኪረፍድ እተኛለሁ:: ስጠጣም ጨልጬ እጠጣለሁ:: የአቡ ዘርዕ እናትን ለማወደስ ምን ማለት ይቻላል? ትልልቅ ቦርሳዎቿ ሁሌም በሪዝቅ የተሞሉ ናቸው:: ቤቷ ሰፊ ነው::

የአቡ ዘርዕ ወንድ ልጅን እንዴት ማወደስ ይቻላል? ትንሽ የጠቦት ፍየል ሥጋ ያጠግበዋል:: የአቡ ዘርዕ ሴት ልጅ ለአባትና እናቷ ታዛዥ ናት:: የአቡ ዘርዕ ባሪያ ስለ አቡ ዘርዕ ባሪያ ምን ብዬ ልንገራችሁ? ምስጢራችንን ትጠብቃለች:: ንብረታችንን አታባክንም:: ቤቱን በንጽህና ትይዛለች::

ይህ ነው የረጅሙ ታሪክ መጨረሻ::

ነቢዩ የተወዳጅ ሚስታቸውን የዓኢሻን ትረካ አዳምጠው ከጨረሱ በኋላ **"አቡ ዘርዕ ለኡሙ ዘርዕ ጥሩ እንደሆነው ሁሉ እኔም ላንቺ እንደሱ ነው"** አሏት::

**ወንዶች ሆይ! እናንተስ ለሚስቶቻችሁ ምን ዓይነት ባል ናችሁ?**

# ትሰሩት በነበረው ደንትን ወረዳችሁ

ከታቢዓይ እንስሶች መካከል አንዷ ቤቷ በራፍ ላይ ተቀምጣ ጸጉሯን ስትታጠብ ዓለ ድመት የማቢውን በር ገፋ ከፈተውና እንድ መንገድ ጸጉሯን አየጣት። በድንገጡ አይጦቹም ወደ ቤት ገቡና ጸጉሯን ተላጩቸው። ጓደኞቿም ሁሉ እንደተላጩቸው ሲጠይቋት እንዲህ በማለት መለሰችላቸው።

"እጅ ላይ ያለው ጸጉር እግሩ ላይ እንዲቀመጥ
አልፈልግም"

# አላህን እንወዳለን ባዮች በበዙ ጊዜ

ጀነትን ተወዳና ዋጋዋ ተሰቅሎ ደሀዎች ተስፋ እንዲቆርጡባት፣ ረከሳና ደረጃዋ ወርዶ በየመንገዱ ማንም እንዲሸምታት አልተደረገም:: በትልቁ የንግድ ስፍራ ለጨረታ ቀርባለች:: ዋጋዋ ነፍስን መሰዋዕት ማድረግ ነው አይቀንስም በተባለ ጊዜ ለነፍሶቻቸው የሚሰስቱ ወደኋላ ቀሩ:: የአላህ ወዳጆች ዋጋው ይቀመስ ከሆነ ለመሸመት ቆመው ይጠባበቁ ጀመር:: እቃው በመሀከላቸው ተዟዟረ:: በእነዚያ ለሙእሚኖች አዛኝ በከሀዲያኖች ላይ ብርቱ በሆኑት ምዕመናን እጅ ወደቀ::

አላህን እንወዳለን የሚሉ ሰዎች በበዙ ጊዜ ለመውደዳቸው ማረጋገጫና ማስረጃን ያመጡ ዘንድ ተጠየቁ"

قُلْ إِن كُنتُمْ تُحِبُّونَ اللَّهَ فَاتَّبِعُونِي يُحْبِبْكُمُ اللَّهُ [٣:٣١]

**"አላህን የምትወዱ ከሆነ ተከተሉኝ እሱም አላህ ይወዳችኋል በላቸው"** (አሊ-ዒምራን፡ 31)

ፍጥረታት በሙላ ወደኋላ ተንፏቀቀ ረሱልን صلى الله عليه وسلم በሥራቸው በንግግራቸውና በሥነ-ምግባራቸው የሚከተሉ ሰዎች ብቻ

ባሉበት ቦታ ቆሙ:: ለእነርሱም "የማስረጃችሁን ትክክለኛነት የሚያጣራ ተግባር እንፈልጋለን" ተባሉ:-

يُجَاهِدُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ وَلَا يَخَافُونَ لَوْمَةَ لَائِمٍ

[٥:٥٤] {مَائِدَة}

"በአላህ መንገድ ላይ ይታገላሉ የወቃሽን ወቀሳ አይፈሩም"

(ማእዳህ 5:54)

አብዛኛዎቹ ወዳድ ነን ባዮች አፈገፈጉ:: በአላህ መንገድ ላይ የሚታገሉ ብቻ ቀሩ ለእነርሱም እንዲህ ተባሉ "የወዳጆች ነፍስና ገንዘብ የነርሱ አይደለምና በሉ ኑ ወደ መገበያያ ሥፍራው"

إِنَّ اللَّهَ اشْتَرَىٰ مِنَ الْمُؤْمِنِينَ أَنفُسَهُمْ وَأَمْوَالَهُم بِأَنَّ لَهُمُ الْجَنَّةَ ۚ يُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ فَيَقْتُلُونَ وَيُقْتَلُونَ ۖ وَعْدًا عَلَيْهِ حَقًّا فِي التَّوْرَاةِ وَالْإِنجِيلِ وَالْقُرْآنِ ۚ وَمَنْ أَوْفَىٰ بِعَهْدِهِ مِنَ اللَّهِ ۚ فَاسْتَبْشِرُوا بِبَيْعِكُمُ الَّذِي بَايَعْتُم بِهِ ۚ وَذَٰلِكَ هُوَ الْفَوْزُ الْعَظِيمُ [٩:١١١]

"አላህ ከምእምናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነት ለነሱ ብቻ ያላቸው በመኾን ገዛቸው፤ በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ፤ ይገድላሉም፤ ይገደላሉም፤ በተውራት በኢንጂልና በቁርኣንም (የተነገረውን) ተስፋ በእርሱ ላይ አረጋገጠ፤ ከአላህም የበለጠ በኪዳኑ የሚሞላ ማን ነው? በዚያም በርሱ በተሻሻጣችሁበት ሽያጫችሁ ተደሰቱ፤ ይህም እርሱ ታላቅ ዕድል ነው " /አት-ተውባ:111/

የገገርውን ትልቅነት የዋጋውን አትራፊነትና ይህ ግብይይት ተፈፃሚነቱ በማን እጅ እንደሆነ ባወቁ ጊዜ ነፍሳቸውና ገንዘባቸውን በርካሽ ተታለው ለሌላ ላለመሸጥ ተጠነቀቁ:: የተከበረውንም ግብይይት በሙሉ ስምምነት ፈፀሙ::

ሸያጩ ተፈፅሞ ውሉ ፀድቆ ነፍሳቸውና ገንዘባቸውን እንዳስረከቡ እንዲህ የሚል አዋጅን ሰሙ:-

**"ነፍሳችሁና ገንዘቦቻችሁ ለእኛ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ አጥፍ ድርብ አድርገን እንመልስላችኋለን ትርፋችሁንም እናስረክባለን"**

**“ وَلَا تَحْسَبَنَّ الَّذِينَ قُتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ أَمْوَاتًا ۚ بَلْ أَحْيَاءٌ عِندَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ “** {٣:١٦٩}

***"እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው:: በርግጥ እነርሱ ጌታቸው ዘንድ ሕያዋን ናቸው፤ ይመገባሉ"***

# አትሌቱ አሞራ

ኢብራሂም ኢብኑ አድሃም የገጠመውን አስገራሚ ክስተት እንዲህ በማለት ያወጋናል፡-

"ሐጅ ለማድረግ በመጓዝ ላይ ሳለሁ ምግብ የያዘ አገልግሎን አሞራ ይዞብኝ ከነፈ:: ጾሜን መዋሌ አሳስቦኝ እሱ በሰማይ እኔ በምድር ዓይኔን እንጋጥጬ እከተለው ጀመር ከርቅትም ወደ አንድ ዋሻ ሲገባ አየሁት ተከትዬው ገባሁ:: አንድ ዕድሜው ገፋ ያለ እዛ ዋሻ ውስጥ ብቻውን እግርና እጁ ታስሮ የኔን ምግብ አቀርቅሮ በአፉ እንደ ዶሮ ሲመገብ ተመለከትኩት:: ማን እንዳሰረው ለምን እንደታሰረም ጠየቅኩት:: እሱም እንዲህ በማለት መለሰልኝ፡- ሐጅ ለማድረግ በወጣሁበት ሽፍቶች ንብረቴን ዘርፈው እንደምታየው እጅና እግሬን አስረው በዚህ በረሃ ላይ ጥለውኝ ሄዱ:: ጌታዬ ሆይ! አንተኑ ለመገዛት ከቤቴ ወጥቻለሁና የሪዝቁን ነገር አደራ በማለት ተማጸንኩት:: እጄን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጌ ዱዓዬን ለጌታዬ አላህ አደረስኩ:: ይሄው እንደምታየው ይህን አሞራ ሰበብ አርጎልኝ ቁርሴንም ምሳዬንም እያመጣ ይመግበኛል::

እናም ወዳጃችን ተወኩል ከሰብብያ ጋር ሲገናኝ የማይሰራው ተዓምር የለምና አንተም ሑረል ዐይኗ ላይ አደራ!

‹‹ ብዕሬን አድምቼ ብፅፍም ስላንቺ

ቃላት ተቆላልፈው ያጡብኛል ፍቺ››

ተጠናቀቀ!!!

## ዋቢ መጽሐፍት

مع الحور........ يحي آل شلوان

يوم فى الجنة..........محمود المصرى

الفائزون بحور العين.......محمود المصرى

صفة الحور العين ..........أم حبيبة

الجنة دار المنقين..............هند بنت عبد العزيز

الحور العين..................... تشوان الحموى

ጀነት እንገናኝ

አልሙልተቀል ጀናህ ከሚለው የሸይኽ ኻሊድ ራሺድ ሙሀደራና ካነበብኳቸው ቆየት ያሉ ምንጫቸውን የማላስታውሳቸው መፅሐፎችና መጣጥፎች::

2011 E.C

1439 ዓ. ሒ.

........አሁን የደነቱን በር መክፈት
በመጠባበቅ ላይ ነን እንደ መሳሺካ
በእንግዶች መምጣት ፊቱ በደስታ ፈክቶ
ይታያል በእጁ የበረን ቅልፍ ይዟል፡፡

........በሩ ተከፈተ የእሳህ ባሮች
ከመሳሺካዎች በሚሰነዘርላቸው ሰላምታ
እየታጀቡ ወደ ውስጥ በመግባት ላይ
ናቸው ከበስተቀኛቸው ካማረ ስል የተሰሩ
ህንፃዎች ይታያሉ ከበስተግራ በኩል
ከወተት የነፃ ፏፏቴ ይፈሳል፡፡

በፏፏቴው ዙሪያ ሑረል ዐይናች መስመር
ሰርተው ቀመው የባሎቻቸውን መምጣት
በጉጉት በመጠባበቅ ላይ ናቸው.......

ኑ!! ተከተሉን

ከመፅሀፉ የተወሰደ